የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፳፻፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25[th] Year No.73
ADDIS ABABA 22[nd] July, 2019

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፶፫/፳፻፲፩ ዓ.ም

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጂኦተርማል ሀብት ልማት ደንብ........................................ገጽ ፲፩ሺ፫፻፲፱

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፶፫/፳፻፲፩ ዓ.ም

### ስለ ጂኦተርማል ሀብት ልማት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፳፻፲፩ አንቀጽ ፭ እና በጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፩/፳፻፰ አንቀጽ ፵፯ (፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጂኦተርማል ሀብት ልማት ደንብ ቁጥር ፬፻፶፫/፳፻፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፡

፩/ "አዋጅ" ማለት የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፩/፳፻፰ ነው፡

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡

## Content

Regulation No.453/2019

Geothermal Resource Development Council of Ministers Regulations........................Page 11,319

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No.453/2019.

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE GEOTHERMAL RESOURCE DEVELOPMENT

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2011 Article 5 and Article 47 (1) of the Geothermal Resource Development Proclamation No. 981/2016.

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Geothermal Resource Development Council of Ministers Regulations No.453/2019."

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1/ "Proclamation" means the Geothermal Resources Development Proclamation No. 981/2016;

2/ The definitions provided on in Article 2 of the Proclamation shall have that meaning.

፫/ "ኃይል የማመንጨት ፈቃድ" ማለት የጂኦተርማል ሀብትን በመጠቀም ኤሌክትሪክ ለማምረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፬/ "ፍሎው ቴስት" ማለት በጂኦተርማል ምርመራ ሥራ ወቅት የቁፋሮ ሥራ ከተከናወነ በኋላ የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻው ሁኔታና የጂኦተርማል ፈሳሽ የማውጣት አቅም ለመገመት የሚከናወን የአሰራር ሂደት ነው፤

፭/ "የቁፋሮ እቅድ" ማለት ፕሮጀክቱን ለማልማት የሚዘረጋ አጠቃላይ የመሠረተ ልማት አውታሮች እና ሕንጻን፣ ይዞታን፣ ተያያዥ ኢንስታሌሽንና መሣሪያዎችን ጨምሮ መንገዶችን፣ ፓይፕላይን፣ ጉድጓዶችን እና የውሃ መገኛና ማከማቻዎችን የሚያብራራ ዕቅድ ፕሮግራም ነው፤

፮/ "የቁፋሮ ፕሮግራም" ማለት ባለፈቃዱ በፈቃድ ይዞታው ባለው የጂኦተርማል ክምችት የሚያከናውነውን የቁፋሮ ሥራን እና ሙከራን በተመለከተ የሚያብራራ ፕሮግራም ሲሆን በፈቃድ ቦታው ከአንድ በላይ የሆኑ የቁፋሮ ሥራ የሚከናውንባቸው እና የጉድጓድ መደቦችና ለማልማት የሚጠበቁ ጉድጓዶችን ዕቅድ አካቶ የያዘ ፕሮግራም ነው፤

፯/ "የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ" ማለት በባለፈቃዱ አጠቃላይ የጉድጓድ ቁፋሮ አሰራር ላይ የታቀደውን ንድፍ የሚያብራራ ሲሆን በተጨማሪም ቁፋሮን፣ ሎጊንግ፣ የሙከራ ሥራ እና የእያንዳንዱ ጉድጓድ የቁፋሮ ሥራ ማጠቃለያን ያካትታል፤

፰/. "የቁፋሮ ይሁንታ ፈቃድ" ማለት በቁፋሮ ፕሮግራሙ መሠረት ለእያንዳንዱ ጉድጓድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፱/ "ኮንሴፕሽዋል ሞዴል" ማለት በጂኦሎጂ፣ ጂኦኬሚስትሪና ጂኦፊዚክስ በተገኙ ጥናቶች መሠረት የሪዘርቮሩ ሙቀትና ግፊት፣ ሪቻርጅ ዞን፣ የሪዘርቮር ጸባይና የሪዘርቮር ፈሳሹ የኬሚካል ይዘቱ መረጃ በመጠቀም የሙቀቱን ምንጭ፣ የሪዘርቮሩ ሙቀትና ግፊት እና በውስጡ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲሁም የተገመተው ሪዘርቮሩ መጠንን የሚያሳይ ሞዴል ነው፤

3/ "Power Generation License" means a license issued to generate electricity using geothermal resources;

4/ "Well Test" means a process of identifying critical reservoir properties used for geothermal exploration to estimate the flow rate, temperature, pressure as well as water quality and capacity of a geothermal reservoir and conducted after drilling has been done;

5/ "Drilling Plan" means the overall program which describes the infrastructure and facilities proposed for development of the project, including roads, pipelines, wells, sumps, water source development and water storage facilities;

6/ "Drilling Program" means a program that describe how the Licensee will drill for and test the geothermal resources covered by its license. The program may include multiple locations at which the Licensee proposes to drill within the license area, and describes the number of well pads and number of wells that are anticipated to be developed;

7/ "Well Design Plan" means is a proposed design that describes all the operational aspects of the Licensee's proposal to drill, including drilling, logging, testing and completion of each individual well;

8/ "Drilling Permit" means is a permit issued by the Licensing Authority for each individual well in accordance with drilling program;

9/ "Conceptual Model" means is a model constructed based on geological, geochemical and geophysical information, temperature and pressure data, information on reservoir properties as well as the chemical content of reservoir fluids which explain the heat source for the reservoir in question and the location of recharge zones, the location of the main flow channels, the general flow patterns within the reservoir as well as reservoir

፲/ "ሎግኢንግ" ማለት በሥነምድር ጥናት ጊዜ በጉድጓድ ቁፋሮ ወቅት በጂኦፊዚክስ ሥራ ወይም ከጉድጓድ የወጣ የኮር ናሙና ተፈጥሮዊ አቀማመጡን የመርመርና የማጤን ሂደት ነው፤

፲፩/ "ግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም" ማለት ቢያንስ ፳፬ (ሃያ አራት) ሳተላይቶችን በመጠቀም ያለንበትን ቦታ ለማወቅ የሚረዳን መሳሪያ ነው፤

፲፪/ "ሪዘርቮር" ማለት በመሬት ውስጥ የሚገኝ የጂኦተርማል ፈሳሽ መያዝ የሚችለው የድንጋይ ስብስብ ነው፤

፲፫/ "ኬዚንግ" ማለት የጉድጓድ ቁፋሮ ከተከናወነ በኋላ ተደርምሶ ጉድጓዱ እንዳይደፍነው የሚከናወን ሥራ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ፈቃድ

### ምዕራፍ አንድ

### የደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ

**፫. ለቅኝት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

፩/ የቅኝት ፈቃድ ለማግኘት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡

ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

(፩) ሙሉ ስሙን፣ ጾታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፤

(፪) ሙያውን፤

(፫) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤

(፬) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፤

temperature and pressure conditions and further provide an estimate of the size of the reservoir involved;

10/ "Logging" means the study of the stereography and geology of the well in the geothermal exploration drilling activity in geophysical survey or core sampling of the well;

11/ "Global Positioning System" is a satellite-based navigation system made up of at least 24 satellites;

12/ "Reservoir" means a volume of rocks in the sub surface which stores geothermal fluids;

13/ "Casing" is an activity of Prevention of loose formation material from collapsing into and blocking the hole of after drilling activities is conducted.

## PART TWO
## LICENSE

### Chapter One

### Grade I Geothermal Resours Licenses

**3. Application for Reconnaissance License**

1/ An application for a Reconnaissance License shall be made to the Licensing Authority in writing on the prescribed form and accompanied by the prescribed application fees, and shall include the following documents:

a) Where the applicant is a natural person:

(1) full name, nationality, gender, age, place and date of birth;

(2) profession;

(3) country of residence and address, telephone number, and email address;

(4) if the applicant is a foreigner, a license authorizing the carrying on of business in Ethiopia;

(፭) ፍቃድ የተጠየቀበትን ቦታና የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮርዲኔት የያዘ አካባቢያዊ ገፅታውንና ስነ-ምድራዊ ተፈጥሮ አቀማመጡን፣ በመሬት ላይ የሚታዩ ቅሪቶችና ስነ-ምድራዊ ለውጦች የሚያሳይ የተቀናጀ ካርታ፣

(፮) በፍቃድ ዘመኑ ወቅት አመልካቹ ሊያከናውን ያቀደው የሥራፕሮግራም፣

(፯) በፈቃድ ክልል ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች፣ አርብቶአደር ማህበረሰቦችን ጨምሮ የሚኖሩትን በመለየት በፈቃድ ቦታው አካባቢ ለመከናወን የታቀዱ ሥራዎች ላይ በማተኮር; በአካባቢ ማህበረሰቦች ላይ የሚያስከትሏቸው ተፅእኖዎች እና ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የቀረበ እቅድ፣

(፰) ማንኛውም በመሬት ላይ ለሚደርስ ተፅዕኖዎች የሚደረግ የማስተካከያ እቅድ፣ እና

(፱) በሥራ ፕሮግራሙ ውስጥ የተገለፀውን ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ከቴክኒክና የገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ መረጃ፡፡

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ፡-

(፩) ስሙ፣ዜግነቱን፣የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ እና ዋና የንግድ ቦታ፣

(፪) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

(፫) አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የአመልካቹ ወኪል ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

(፬) አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣ እና

(5) the map of the area proposed to be covered by the license including global positioning system coordinates, integrated map and description of the physical characteristics and its surrounds, including geology, surface manifestations fossil manifestation, areas of alteration and major geological structures;

(6) the proposed work program the applicant proposes to carry out during the term of the license;

(7) identification of human habitation and communities in the proposed license area including nomadic communities, focusing on areas where proposed activities will take place under a license; impacts on local communities and proposed mitigation plan on how to address such impacts;

(8) a plan for the restoration of any surface disturbance; and

(9) information and evidence showing the technical and financial capacity of the applicant to carry out the work identified in the work program.

b) Where the applicant is a juridical person:

(1) its name, nationality, legal form, nature of business and principal place of business;

(2) address of its head office, telephone number, and email address;

(3) name, address, telephone number, and email address of the applicant's designated agent or representative in Ethiopia certified by the appropriate government organization;

(4) copies of its memorandum and articles of association duly certified by the appropriate government organization;

(፭) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ(ሀ) ስር ከንዑስ አንቀጽ (፬) እስከ ንዑስ አንቀጽ (፱) የተጠቀሱትን ዝርዝር መረጃዎች፡፡

፪/ አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተጠቀሱ መረጃዎች በተጨማሪ ፈቃድ በተጠየቀበት ቦታ ውስጥ የተካተተውን አካባቢ ለመለየት፡ ስለ ቦታው በማጣራትና አሳማኝ የትንታኔ መረጃዎችን ያካተተ የሚከተሉትን የያዘ ዕቅድ ሊያቀርብ ይችላል፡-

ሀ) የቦታውን አቀማመጥ፡ ስነ ምድራዊ ገጽታ፡ በመሬት ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ክስተቶች የሚገልፅ ጂኦሎጂካል ካርታ፡

ለ) ከውሀ እና ከጋዝ ናሙና የተገኘ የሙቀት መጠን የሚገልፅ መረጃ፡

ሐ) ማንኛውም ከጂኦፊዚክስ ስራ የተገኘ የጥናት ውጤትና ካርታ፡

መ) ወደ ፍቃድ ቦታው ለመድረስ የሚጠቀምበት መንገድ፡ እና

ሠ) አመልካቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የያዘው ወይም ከዚህ በፊት ይዞ ሲንቀሳቀስበት የነበረ የጂኦተርማል ፍቃድ ካለ፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀፅ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ ሊቀርቡ የሚገባቸው ሌሎች መረጃዎች በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

## ፬. ለምርመራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ የምርመራ ፈቃድ ለማግኘት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡

ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

(፩) ሙሉ ስሙን ፤ ዖታውን ፤እድሜውን፤ ዜግነቱን፤የትውልድ ቀንና ቦታ፡

(፪) ሙያውን፡

(፫) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፡

(፬) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፡

(5) particulars stated from (4) to (9) under Sub-Article (1) (a) of Article 3 of this Regulation.

2/ In addition to the information requested in Sub-Article (1) of this Article, the applicant should include a proposal for delineation of the area proposed to be covered by the license, with preliminary analysis of information justifying the requested License Area:

a) geological maps of the area, indicating location of major structural features and manifestation areas of alteration;

b) geothermometer temperatures based on water and gas sampling;

c) interpretation of any geophysical surveys conducted, including any maps;

d) proposed access road which takes to the License Area; and

e) any geothermal license the applicant currently holds or has previously held in Ethiopia.

4/ In addition to the information requested in this Article, the Licensing Authority may request additional information to be determined by the directives.

## 4. Application for an Exploration License

1/ An application for an Exploration shall be made in writing on the prescribed form and, accompanied by the prescribed application fees, and shall include the following documents:

a) Where the applicant is a natural person:

(1) full name, nationality, gender, age, place and date of birth;

(2) profession;

(3) country of residence and address, telephone number, and email address;

(4) if the applicant is a foreigner, a license authorizing the carrying on of business in Ethiopia;

(፭) ፈቃድ የተጠየቀበትን ቦታና የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮርዲኔት የያዘ አካባቢያዊ ገፅታውንና ስነምድራዊ ተፈጥሮ አቀማመጡን፣ በመሬት ላይ የሚታዩ ቅሪቶችና ስነ-ምድራዊ ለውጦች የሚያሳይ የተቀናጀ ካርታ፣

(፮) አመልካቹ አካባቢው እንዴት እና ለምን ለጂኦተርማል ልማትና ጥቅም አቅም እንዳለው ሊያሳምነው የቻለውን አጠቃላይ መረጃ፣

(፯) የጤንነት፣ የደህንነት፣ የአካባቢ እና የማህበረሰብ ልማት ተገዢነትን የማረጋገጥ ሀላፊነት ያለባቸው ሰራተኞች ስም እና የሚገኙበት መረጃ፣

(፰) ለታቀደው የምርመራ ሥራ የመነሻ ሁኔታዎችን የሚያሳይ የፀደቀ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ፣

(፱) አመልካቹ ፕሮጀክቱን ለማከናወን የቴክኒክ፣ የገንዘብ አቅም እና ልምድ እንዳለው የሚያሳዩ መረጃዎች፡፡

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ፡-

(፩) ስሙ፣ ዜግነቱን፣ የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ እና ዋና የንግድ ቦታ፣

(፪) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

(፫) የአመልካቹ በኢትዮጵያ ተወካይ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የተወካይ ኢሜይል አድራሻ፣

(፬) አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣

(፭) የድርጅቱ ዋና ኃላፊዎች ስም፣ ዜግነት፣ የሥራ ልምድ፣ በተጨማሪም ዳይሬክተሮችና ኃላፊዎች እና የሕግ ሰውነት ያለው አካል ካፒታል ድርሻ

(5) the map of the area proposed to be covered by the license including global positioning system coordinates, integrated map and description of the physical characteristics and its surrounds, including geology, surface manifestations fossil manifestation, areas of alteration and major geological structures;

(6) a full summary of information available to the applicant that describes how and why the applicant believes that the area has the potential for geothermal development and use;

(7) names and contact information for personnel responsible for ensuring health and safety and environmental and social compliance;

(8) an approved environmental and social impact assessment covering planed exploration activities and including baselines study;

(9) information and evidence showing the applicant's technical and financial capability and experience in carrying out the project; and

b) Where the applicant is a juridical person:

(1) its name, nationality, legal form, nature of business and principal place of business;

(2) address of its head office; telephone number, and email address;

(3) name, address, telephone number, and email address of the applicant's designated agent or representative in Ethiopia;

(4) copies of its memorandum and articles of association duly certified by the appropriate government organization;

(5) the name, nationality and experience of key personnel, including every director or equivalent officer, and, if the juridical person holds a capital

ካለው ከ፭% በላይ ድርሻ ያለው ማንኛውም ሰው፤

(፮) የዳይሬክቶሮች ቦርድ ስም ዝርዝር አድራሻና ዜግነት፤

(፯) በአመልካቹ ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠው ሰው ስም እና የሥራ ድርሻ፤ እና

(፰) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ(ሀ) ስር ከንዑስ ንዑስ አንቀፅ (፬) እስከ (፱) የተጠቀሱትን ዝርዝር መረጃዎች፡፡

፪/ የምርመራ ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርበው የሥራ ፕሮግራም የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) በመጀመሪያ ዓመት የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎች ዝርዝር ማብራሪያ፣ በተጨማሪ የሚካሄዱ የቅኝት ሥራዎች ካሉ እንዲሁም የመነሻ ምርመራ ጉድጓድ ለመቆፈር የተለዩ ቦታዎች ካሉ፤

ለ) ቢበዛ በሶስተኛ ዓመት መጨረሻ ድረስ የሚጠናቀቅ የጉድጓድ ቁፋሮ ዕቅድና በአራተኛ ዓመት የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መጀመርን ያካተተ የረዥም ጊዜ የምርመራ ሥራዎች ዕቅድ፤

ሐ) የነባር መንገዶች የሚገኙበትን ቦታ እና አስፈላጊ የሆኑ መንገዶች ለመገንባት የተያዘ ዕቅድ፤

መ) ቁልፍ ለሆኑ ሥራዎች ወጪዎችን ለማሳየት የሚረዳ የፍቃድ ዘመኑ የሥራ ፕሮግራም እና ተያያዥ በጀት፤

ሠ) የጤና እና የደህንነት ዕቅድ፤ እና

ረ) ከአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የትግበራ ኮድ ጋር የሚጣጣም በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የጉድጓድ ቁፋሮ፣ ሙከራ እና ሪፖርት ማድረጊያ ዕቅድ፡፡

፫/ አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተገለፁ መረጃዎች በተጨማሪ ፈቃድ በተጠየቀበት ቦታ ውስጥ የተካተተውን አካባቢ ለመለየት፣ ስለ ቦታው በማጣራትና አሳማኝ የትንታኔ መረጃዎችን ያካተተ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ዕቅድ ሊያቀርብ ይችላል፡-

share, the name of any person who is the beneficial owner of more than five per cent (5%) of the issued capital shares;

(6) a list of the names of the board of directors, showing the address and nationality of each;

(7) the name and title of any person or persons authorized to sign on behalf of the applicant; and

(8) particulars stated from (4) to (9) under Sub-Article (1) (a) of Article 4 of this Regulation.

2/ A proposed work program for an application for Exploration License shall have the following information:

a) a detailed description of the activities to be carried out in the first year of exploration, including any additional reconnaissance work to be carried out and, if known, location of preliminary exploration wells;

b) a description of the long-range plan for exploration activities, including a plan for completion of a drilling plan by the end of the third year the latest, with drilling to start by the fourth year the latest;

c) location of existing access roads, and plans for construction of any roads that may be needed;

d) a work plan and associated budget for the license term showing expenditures on key items;

e) a health and safety plan; and

f) a well drilling, testing and reporting plan Directives to be issued in accordance with the African Union Code of Practice for Geothermal Drilling.

3/ In addition to the information requested in Sub-Article (1) of this Article, the applicant should include a proposal for delineation of the area proposed to be covered by the license, with preliminary analysis of information justifying the requested License Area,

ሀ) ዋና ዋና የጂኦሎጂ እና ስትራክቸራል ባህርያት፣ በመሬት ላይ የሚታዩ ለውጦችን የሚያሳይ የፍቃድ ቦታውንና አካባቢውን የሚገልፅ የጂኦሎጂ ካርታ፤

ለ) በቦታው የተከናወኑ የጂኦኬሚካል ሰርቬይ ጥናቶችና ትንታኔዎችን የሚያሳይ እና የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻው ባህርያትና ሊኖር የሚችለው ሀብት ሙቀት መጠን መግለጫ፤

ሐ) ማንኛውም ከጂኦፊዚክስ ሥራ የተገኘ የጥናት ውጤት፣ ጂኦፊዚካል ክሮስሴክሽንና ካርታ፤

መ) ወደ ፍቃድ ቦታው ለመድረስ የሚጠቀምበት መንገድ፤

ሠ) የፍተሻ ጉድጓዶች ሊቆፈሩ የሚችሉባቸው ቦታዎችን የሚሳይ ካርታ፤

ረ) በእያንዳንዱ የጥናት ደረጃ ላይ የተሳተፉ ሰዎች ስም፣ የጂኦተርማል ምርመራ ሥራ ላይ ያላቸው ብቃትና ልምድ የሚገልፅ ማብራሪያ፤

ሰ) የዳይሬክተሮች ቦርድ የቅርብ ጊዜ ዓመታዊ ሪፓርት፤ እና

ሸ) የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች ሰነድ እና የባለፉት ፫ (ሦስት) ዓመታት የኦዲተሮች ሪፖርቶች ቅጂ፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀፅ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ ሊቀርቡ የሚገባቸው ሌሎች መረጃዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

## ፭. <u>የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፍቃድ ማመልከቻ</u>

፩/ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡

ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

(፩) ሙሉ ስሙን፣ ፆታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፤

(፪) ሙያውን፤

(፫) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤

a) geological maps of the license and surrounding areas, indicating location of major geological and structural features, surface manifestation areas of alteration;

b) description of geochemical surveys undertaken and analyses that may indicate reservoir fluid properties and potential resource temperatures;

c) description and interpretation of any geophysical surveys conducted, including any maps and geophysical cross-sections;

d) proposed access road which takes to the License Area;

e) if sufficient data are available, an indication of the potential location of exploratory wells;

f) identification of the persons who undertook each stage of the surveys and/or interpretations and a brief description of their geothermal exploration qualifications and experience;

g) the latest annual report of the board of directors, if any;

h) copies of balance sheets, profit and loss statements and auditor's reports for the previous three years, if any.

4/ In addition to the information requested in this Article, the Licensing Authority may request additional information to be determined by the directives.

## 5. <u>Application for Well-Field Development and Use License</u>

1/ An application for a Well-field Development and Use License to the Licensing Authority shall be made in writing on the prescribed form and accompanied by the prescribed application fees, and shall include the following documents:

a) Where the applicant is a natural person:

(1) full name, gender, age nationality, place and date of birth;

(2) profession;

(3) country of residence and address, telephone number, and email address;

(፬) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፤

(፭) ፈቃዱ ለምን ያህል ጊዜ እንደተፈለገ፣

(፮) የጂኦተርማል ሀብቱ ሙቀት፣ ፈሳሽ የማሳለፍና የመያዝ እና የጂኦተርማል የግፊት መጠን አቅሙ፣ እንዲሁም ከጉድጓድ የተገኘ የውሃ ኬሚስትሪ መረጃ፤

(፯) ፈቃዱ የተጠየቀበትና ሥራው ሊካሄድ የታሰበበት ቦታድንበር መታጠፊያዎችን ጭምር የሚያሳይ ጂኦሜትሪያዊ ቅርፅ ያለው የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስቲም፣ ጂኦግራፊክ ኮርዲኔት እና አመላካች የሆነ የመሬት ላይ ምልክቶች፣ መልካ ምድራዊ እና አካላዊ ገፅታ የሚያሳይ ካርታ፤

(፰) የጂኦተርማል ክምችቱ ምን ያህል ጥልቀት እና ስፋት እንዳለው የሚያሳይ የመነሻ ፅንሰ-ሃሳብ ሞዴልና ሊኖር የሚችል የክምችት መጠን፣ የጂኦተርማል ክምችቱ ፀባይ፣ ስፋቱንና መጠኑን በተሻለ ለማረጋገጥና የበለጠ ለማብራራት የሚጠቀምበትን መንገድ የሚያሳይ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት ፕሮግራም ሪፖርት፤

(፱) በፈቃድ ቦታው ያሉና የታቀዱ ጉድጓዶች፣ እንፋሎቱን ማሰባሰቢያ ዘዴዎች፣ የጂኦተርማል ሀብቱን ለማልማት እና ለመጠቀም የሚያስችሉ ህንፃዎችና ንብረቶች፣ በቀጣይ ቁፋሮና ልማት ወቅት ዕቅዱ ሊሻሻል እንደሚችል ታውቆ በቦታው ያሉና የሚገነቡ አገልግሎት መስጫዎች ዕቅድ ጨምሮ በቦታውና ከቦታው ውጭ የሚደረግ ማሻሻያዎች ዝርዝር፤

(፲) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚጠይቀው መሠረት የሚጠበቀው ዲስቻርጅና ኢንጄክሽን፣ የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ሪዘርቮር ፀባይ፣ የጂኦተርማል ሀብት ምርት እና ትንተና፤

(4) if the applicant is a foreigner, a license authorizing the carrying on of business in Ethiopia;

(5) the duration for which the license is sought;

(6) well data characterizing the geothermal resource temperature and permeability, pressure and complete water chemistry;

(7) a map of the proposed license area, at an appropriate scale, indicating the geographical coordinates of the turning points along its boundaries using global positioning system coordinates, and showing all important landmarks, and topographic and other physical features;

(8) a preliminary conceptual model of the resource that shows estimated depth and extent of the probable reservoir; and a report explaining the approach the applicant will use to better define the existence, size, and characteristics of the reservoir through its well-field development program;

(9) a site plan showing existing and proposed wells, steam gathering systems, buildings and other facilities for development and use under the license, and details of use of existing infrastructure and plans for construction of new infrastructure, including onsite and offsite improvements, recognizing that the plan may be modified as the resource is further drilled and developed;

(10) a description and analysis of anticipated reservoir production, discharge and injection, and reservoir characteristics to the extent required by directives of the Licensing Authority;

(፲፩) ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ጨምሮ በፈቃድ ዘመኑ የመጀመሪያ ሁለት ዓመታት የሚከናወኑ ዝርዝር የሥራ ፕሮግራምና በጀት እና ለቀሪው የፈቃድ ዘመን የበጀት ዕቅድ፤

(፲፪) በአመልካቹ ለህብረተሰቡ የተደረገ የአገልግሎት፣ የእርዳታና የማስተባበር ሥራ ካለ እንዲሁም ከአከባቢው ህብረተሰብ ጋር በመተባበር የሚመጣውን ተፅእኖ ለመለየትና ለመፍታት የታቀደ ዕቅድ፤

(፲፫) አግባብ ባላቸው የክልል ባለስልጣናት የፀደቁ የማህበረሰብ ልማት እቅዶች፤

(፲፬) የካፒታል እና የሥራ ማስፈጸሚያ ወጪዎች ትንበያና እንዲሁም የፕሮጀክቱን የፋይናንስ አዋጭነት የሚያሳይ የበጀት ምንጭ እና የፋይናንስ እቅድ፤

(፲፭) የኢትዮጵያ ዜጎችን ቅጥርና ሥልጠና በተመለከተ የቅጥር እና የሥልጠና ፕሮግራሞች፤

(፲፮) በሚመለከታቸው ሕጎች መሠረት የፀደቀ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ሪፖርት፤

(፲፯) ለጂኦተርማል ሥራ የሚያስፈልጉ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ እቃዎችና አገልግሎቶች፣ ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ከውጪ የሚገቡ እቃዎችና አገልግሎቶች እና እነዚህ እቃዎችና አገልግሎቶች በሥራ ላይ እንዴት እንደሚውሉ የሚያሳዩ ዕቅዶች፤

(፲፰) የጂኦተርማል ሥራው በሚዘጋበት ጊዜ የጉድጓዶችን መድፈንና መተው እንዲሁም ህንጻዎችንና መገልገያዎችን የማጠር ወይም የማንሳት ዕቅድ፤ እና

(፲፱) የጂኦተርማል ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል የታቀደው ለተቀናጀ ሙቀትና ኃይል ከሆነ፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፬ መሠረት የሚፈለግ መረጃ፡፡

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ፡-

(11) proposed annual work program and budget, including details of work to be performed and budget expenditures for the first two years of the license term; an estimated budget for the remainder of the license term;

(12) community outreach and coordination already undertaken by the applicant, if any, and a plan for coordinating with local communities to determine and address impacts;

(13) plans for community development approved by the appropriate regional State authorities;

(14) projected capital and operating costs, and a financial plan including sources of funding demonstrating the financial viability of the project;

(15) program of employment and training including proposals with respect to the employment and training of citizens of Ethiopia;

(16) an approved environmental and social impact assessment report in accordance with the relevant laws;

(17) goods and services required for geothermal operations which can be obtained within Ethiopia, and goods and services related to the activity to be imported, and the applicant's plans for implementation in relation thereto;

(18) plans for closure of geothermal operations fence, remove buildings and facilities including properly plugging and abandoning of wells; and

(19) if the proposed use of geothermal resources is for combined heat and power, information required under Article 24 of these Regulation.

b) Where the applicant is a juridical person:

(፩) ስሙ፣ ዜግነቱን፣ የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ እና ዋና የንግድ ቦታ፣

(፪) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

(፫) የአመልካቹ በኢትዮጵያ ተወካይ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የተወካይ ኢሜይል አድራሻ፣

(፬) አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣

(፭) የድርጅቱ ዋና ኃላፊዎች ስም፣ ዜግነት፣ የሥራ ልምድ፣ በተጨማሪም ዳይሬይክተሮችና ኃላፊዎች እና የሕግ ሰውነት ያለው አካል ካፒታል ድርሻ ካለው ከ፭% በላይ ድርሻ ያለው ማንኛቸውም ሰው፣

(፮) የዳይሬክተሮች ቦርድ ስም ዝርዝር፣ አድራሻና ዜግነት፣

(፯) በአመልካቹ ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠው/የተሰጣቸው ሰዎች ስም/ስሞች እና የሥራ ድርሻቸው፣ እና

(፰) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ(ሀ) ስር ከንዑስ ንዑስ (፬) እስከ (፲፱) የተገለጹት ዝርዝር መረጃዎች፡፡

፪/ አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተገለጹት መረጃዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊያቀርብ ይችላል፡-

ሀ) አመልካቹ ፈቃድ ለመጠየቅ መሠረት ያደረገውን የምርመራ ፈቃድ የፈቃድ ቁጥር፣

ለ) በሚሰጠው የፈቃድ ቦታ በአመልካቹ የተካሄደ የምርመራ ሥራ ካለ የማጠቃለያ ሪፖርት፣

ሐ) የዳይሬክተሮች ቦርድ የቅርብ ጊዜ ዓመታዊ ሪፖርት ቅጂ፣ እና

መ) የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች ሰነድ፣ እና የባለፉት ሦስት ዓመታት የኦዲተሮች ሪፖርቶች ቅጂዎች፡፡

(1) Its name, nationality, legal form, nature of business and principal place of business;

(2) address of its head office; telephone number, and email address;

(3) name, nationality, address, telephone number, and email address of the applicant's designated agent or representative in Ethiopia;

(4) copies of its memorandum and Articles of Association duly certified by the appropriate government organization;

(5) the name, nationality and experience of key personnel, including every director or equivalent officer, and, if the juridical person holds a capital share, the name of any person who is the beneficial owner of more than five per cent (5%) of the issued capital shares;

(6) a list of the names of the board of directors, showing the address and nationality of each;

(7) the name and title of any person or persons authorized to sign on behalf of the applicant;

(8) particulars stated from (4) to (19) under Sub-Article (1) (a) of Article 5 of this Regulation.

2/ In addition to the information requested in Sub-Article (1) of this Article, the applicant shall include a proposal justifying the requested License Area:

a) the license number of the applicant's Exploration License on which the application is based;

b) a report summarizing exploration work, if any, conducted by the applicant in the proposed License Area;

c) a copy of the latest annual report of the board of directors, if any; and

d) copies of balance sheets, profit and loss statements and auditor's reports for the previous three years, if any.

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ ሊቀርቡ የሚገባቸው ሌሎች ዝርዝር መረጃዎችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ

**፮. የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የመስጠት ስልጣን**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፫(፫) መሠረት ለሚመለከተው የክልል መንግሥት የቀረበ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ማመልከቻን ፈቃድ ሰጪው የክልል መንግሥት ምዝገባ እና የመጀመሪያ ምልከታ ያደርጋል፡፡

፪/ ለሚመለከተው የክልል መንግሥት የቀረበ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ማመልከቻ ፕሮጀክቱ በየዓመቱ ከሁለት ሚሊዮን (፪ሚሊዮን) ኪዩቢክ ሜትርና ከዚያ ያነሰ የጂኦተርማል ሀብት እና አማካይ የሙቀት መጠን ከመቶ ሃያ (፩፻፳) ዲግሪ ሴልሺየስ ወይም ከዚያ በታች ከሆነ የክልሉ መንግሥት በሚደነግገው አሠራር መሠረት ማመልከቻው የሚስተናገድ ሲሆን ለመረጃ አያያዝና ለቅንጅታዊ አሰራር ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከፍቃድ ጥያቄው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለፈቃድ ሰጪው ያጋራል፡፡

**፯. ለደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ**

ለደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

ሀ) ሙሉ ስሙን፣ ፆታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣

ለ) ሙያውን፣

ሐ) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

መ) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፣

3/ In addition to the information requested in this Article, the Licensing Authority may request additional information to be determined by the directives.

## CHAPTER TWO

## GRADE II GEOTHERMAL RESOURCE LICENSES

**6. Authority to Issue Grade II Geothermal Resources Licenses**

1/ Grade II Geothermal Resources License applications submitted to the appropriate Regional Government in accordance to Article 13 (3) of the Proclamation, the appropriate Regional Government shall conduct registration and initial review.

2/ If the submitted Grade II Geothermal Resources License application indicates that the project will utilize a total of two million (2,000,000) cubic meters or less of Geothermal Resources annually and the anticipated temperature of the resource is 120 degrees Celsius or lower, the application will be processed in accordance to the Regional Government provision and for exchange of information and registration all data regarding the application shall be shared to the Licensing Authority.

**7. Application Submitted for the Licensing Authority for Grade II Geothermal Resources License**

An application submitted for a Grade II Geothermal Resources License shall be made in writing to the Licensing Authority on the prescribed form, accompanied by the prescribed application fees, and shall include the following particulars:

1/ Where the applicant is a natural person:

a) full name, nationality, gender, age, place and date of birth,

b) profession;

c) country of residence and address, telephone number, and email address;

d) if the applicant is a foreigner, a license authorizing the carrying on of business in Ethiopia;

ሠ) ፈቃድ የተጠየቀበት ቦታ ይሸፍነዋል ተብሎ የታሰበበትን ሥፍራ የሚያሳይ ካርታ እና የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮርዲኔት እና የቦታውን አስፈላጊነት የሚያሳይ የመጀመሪያ ደረጃ ቅድመ ጥናት፣

ረ) አመልካቹ አካባቢው እንዴት እና ለምን ለጂኦተርማል ልማትና ጥቅም አቅም እንዳለው ሊያሳምነው የቻለውን አጠቃላይ መረጃ፣

ሰ) በፈቃድ ክልል ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች፣ አርብቶ አደር ማህበረሰቦችን ጨምሮ የሚኖሩትን በመለየት በፈቃድ ቦታው አካባቢ ለመከናወን የታቀዱ ሥራዎች ላይ በማተኮር፣ በአካባቢ ማህበረሰቦች ላይ የሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎች እና ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የቀረበ እቅድ፣

ሸ). በፍቃድ ጊዜ ውስጥ.የሚመረቱ ምርቶች፣ የገቢ እና ወጪዎች፣ እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ የሥራ እና የሥልጠና ተጠቃሚነትን የሚጨምር የሽያጭ ዕቅድ፣

ቀ) በመርሃ ግብሩ ውስጥ የተገለጸውን ሥራ ለመፈጸም የሚያስችል ከቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ መረጃ፣

በ) ፈሳሽ ሙቀት ለመለካት የሚያስችል በቂ የሆነ የሙከራ እና የክትትል እቅድ፣

ተ) የሚገመተው ደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ምርት፣ ፍሰትና ሪኢንጀክሽን እና የጂኦተርማል ሀብቱ ጥቅም ላይ መዋል የሚጀምርበት የጊዜ ሰሌዳ ማብራሪያ፣

ቸ) ተፅዕኖን መከላከል ወይም መቀነስን ያካተተ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት፣

ኀ) የኢትዮጵያ ዜጐችን ቅጥርና ሥልጠና በተመለከተ የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራሞች፣ እና

ነ) ለጂኦተርማል ሥራ የሚያስፈልጉ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ እቃዎችና አገልግሎቶች እና ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ከውጪ የሚገቡ እቃዎችና አገልግሎቶች ዕቅዶች፡፡

e) the map of the area proposed to be covered by the license including global positioning system coordinates, and baseline study which shows the importance of the area;

f) a short summary of information available to the applicant that describes how and why the area has the potential for geothermal development and use;

g) identification of human habitation and communities in the proposed license area including nomadic communities, focusing on areas where proposed activities will take place under a license; impacts on local communities and a plan proposed for mitigation of such impacts;

h) business plan including anticipated types of products, revenues and expenses during the license period, and employment and training benefiting the local community;

i) information related to the technical and financial capacity of the applicant to carry out the work identified in the work program;

j) an adequate testing and monitoring plan to measure fluid temperature;

k) a description of anticipated Grade II geothermal resources production, discharge and reinjection and the time frame within which geothermal resource use shall commence;

l) environmental and social impact assessment including a plan for avoiding or mitigating impacts;

m) program of employment and training including proposals with respect to the employment and training of citizens of Ethiopia; and

n) a description of the types of goods and services that will be obtained within Ethiopia and those that will be obtained from outside of Ethiopia.

፪/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ፡-

ሀ) ስሙ፣ዜግነቱን፣የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ፣

ለ) የዋና ቢሮው አድራሻ፣

ሐ) የአመልካቹ በኢትዮጵያ ተወካይ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የተወካይ ኢሜይል አድራሻ፣

መ) አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣

ሠ) የድርጅቱ ዋና ኃላፊዎች ስም፣ ዜግነት፣ የሥራልምድ፣ በተጨማሪም ዳይሬክተሮችና ኃላፊዎች እና የሕግ ሰውነት ያለው አካል ካፒታል ድርሻ ካለው ከአምስት በመቶ (፭%) በላይ ድርሻ ያለው ማንኛውም ሰው፣

ረ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ስም ዝርዝር አድራሻና ዜግነት፣

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከፊደል ተራ (መ) እስከ (ነ) ስር የተጠቀሱትን ዝርዝር ማስረጃዎች፣

ሸ) በአመልካቹ ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠው ሰው ስም እና ሥልጣን፡፡

፫/ አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተገለፁ መረጃዎች በተጨማሪ የሚገኝ ከሆነ ፈቃድ በተጠየቀበት ቦታ ውስጥ የተካተተውን አካባቢ ለመለየት፣ ስለ ቦታው በማጣራትና አሳማኝ የትንታኔ መረጃዎችን ያካተተ ዕቅድና የሚከተሉትን ሊያቀርብ ይችላል፡-

ሀ) የቦታውን አቀማመጥ፣ ቅነ ምድራዊ ገጽታ፣ በመሬት ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ክስተቶች የሚገልፅ ጂኦሎጂካልና ስትራክቸራል ካርታ፣

(፩) ከውሀ እና ከጋዝ ናሙና የተገኘ የሙቀት መጠን ውጤት መግለጫ፣

(፪) ማንኛውም ከጂኦፊዚክስ ስራ የተገኘ የጥናት ውጤትና ካርታዎች፡፡

ለ) የታቀዱ ማሻሻያዎችን የሚያሳይ የቅየሳ ቦታውን የሚያሳይ ዕቅድ፣

2/ Where the applicant is a juridical person:

a) its name, nationality, legal form, nature of business;

b) address of its head office;

c) name, address, telephone number, and email address of the applicant's designated agent or representative in Ethiopia.

d) copies of its memorandum and articles of association duly certified by the appropriate government organization;

e) the name, nationality and experience of key personnel, including every director or equivalent officer, and, if the juridical person holds a capital share, the name of any person who is the beneficial owner of more than five per cent (5%) of the issued capital shares;

f) a list of the names of the board of directors, showing the address and nationality of each;

g) particulars stated from (d) to (n) under Sub-Article (1) of this Article;

h) the name and title of any person authorized to sign on behalf of the applicant.

3/ If the information is available, in addition to particulars stated under Sub-Article (1) of this Article a proposal for delineation of the area proposed to be covered by the license, with preliminary analysis of information justifying the requested License Area, including:

a) geological maps of the license and surrounding areas, indicating location of major geological and structural features, surface manifestation areas of alteration:

(1) geothermometer temperatures based on water and gas sampling;

(2) interpretation of any geophysical surveys conducted, including any maps.

b) site plan showing planned improvements;

ሐ) የዳይሬክተሮች ቦርድ የቅርብ ጊዜ ዓመታዊ ሪፖርት፣

መ) የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች ሰነድ እና የባለፉት ሦስት ዓመታት ኦዲተሮች ሪፖርቶች ቅጂ ካለ፣

ሠ) ወደ ፍቃድ ቦታው ለመድረስ የሚጠቀምበት መንገድ፣

ረ) አመልካቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የያዘው ወይም ከዚህ በፊት ይዞ ሲንቀሳቀስበት የነበረ የጂኦተርማል ፍቃድ ካለ ስለፈቃዱ መረጃ፣

ሰ) በአመልካቹ ለአከባቢው ህብረተሰብ የተሰጠ አገልግሎት ወይም የትብብር ሥራ ካለና እንዲሁም ከአከባቢው ህብረተሰብ ጋር በመተባበር ችግሮችን ለመለየትና ለማስወገድ የታቀደ ዕቅድ፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ምክንያታዊ የሆነ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን በሚወጣ መመሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ፰. የማመልከቻዎች ማስታወቂያ ምዝገባ እና ህትመት

፩/ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና ለሚመለከተው የክልል መንግሥት ለደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ የቀረበ ማንኛውም ማመልከቻ፣ ፍቃድ፣ ዕድሳት፣ ጊዜ ማራዘሚያ፣ ፍቃድ መመለስ፣ መዳረግ ወይም ማንኛውም ዓይነት በዕዳ ማስያዝ ጥያቄ ማመልከቻ በጂኦተርማል መዝገብ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ለማንኛውም ማመልከቻ ጥያቄ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን፦

ሀ) የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ማመልከቻ ስለታቀደው ፕሮጀክት፣አካባቢ እና በመመሪያ በሚወጣው መሠረት ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን አካቶ ሰፊ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ ላይ ያሳውቃል፣

ለ) ማስታወቂያው በጋዜጣ ላይ በወጣ በአስራ አምስት (፲፭) ቀናት ውስጥ ተቃውሞ ካልቀረበ በሚቀጥሉት አስር (፲) የሥራ ቀናት ውስጥ በቴክኒክና ፋይናንስ መስፈርት መሠረት ይገመግማል፣

ሐ) የቴክኒክና ፋይናንስ መስፈርት በዚህ ደንብ መሠረት በመመሪያ ይወጣል፡፡

፫/ አመልካቹ ሁሉንም የምዝገባ እና የህትመት ወጪዎች ይሸፍናል፡፡

c) the latest annual report of the board of directors;

d) copies of balance sheets, profit and loss statements and auditor's reports for the previous three years, if any;

e) proposed access road which takes to the License Area;

f) information about any geothermal license the applicant currently holds or has previously held in Ethiopia;

g) community outreach and coordination activities already undertaken by the applicant, if any, and a plan for coordinating with local communities to determine and address impacts.

4/ any other information as may reasonably be requested by the Licensing Authority to be determined by the directives.

## 8. Registration and Publication of Notice of Applications

1/ Promptly upon receipt the Licensing Authority shall mark each application for Grade II Geothermal Resources License, renewal, extension, surrender, transfer, assignment, or any form of encumbrance with a date of receipt and enter the application in the Geothermal Register.

2/ For any application , the Licensing Authority shall:

a) publish a notice of Grade II Geothermal Resources License application in a newspaper of wide circulation, describing the proposed project, its location and other particulars as provided in directives;

b) within 10 working days of the end for the 15 days notice period, if there are no objections, the Authority concerned shall approve the proposed project, based on technical and financial criteria;

c) the technical and financial criteria shall be set out in directives issued hereunder.

3/ The applicant shall pay all costs for registration and publication.

## ፱. የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ስለመስጠት

፩/ በመመሪያ በሚወሰነው ቅጽና መስፈርት መሠረት የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ለጂኦተርማል ሀብት ቀጥተኛ ጥቅም የሚውል ያለ ውድድር ይሰጣል፡፡

፪/ እንደአግባቡ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ አመልካቹ ከዚህ በፊት የቅኝት ወይም የምርመራ ፈቃድ ሳይኖረው ሊሰጠው ይችላል፡፡

፫/ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ባለፈቃድ ማሟላት ያለበት ዓመታዊ የመለኪያ እና ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች፡-

ሀ) የእንፋሎት እና/ወይም የሞቀ ውሃ ፍሰት፣

ለ) በተቋሙ ውስጥ ያለው ሙቀት፣

ሐ) ከተቋሙ ውጭ ያለው ሙቀት፣ እና

መ) በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያስፈልጉ ተጨማሪ መለኪያዎች እንደ ተቋሙ ዓይነት፣ የጂኦተርማል ሀብቱ ሁኔታና ጥራት እና የማንኛውም የሽያጭ ውሎች፡፡

## ፲. በባለፈቃድ የሚያዝ የፈቃድ ቦታ ስፋት ወሰንና መያዝ የሚቻለው የፈቃድ ቁጥር ብዛት

፩/ በደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ መያዝ የሚገባው የቦታ ስፋትና ወሰን የሚወሰነው ለደረጃ II የጂኦተርማል ስራ የሚያስፈልግ ቦታ እና በባለፈቃዱ ፕሮጀክት በሚቀርበው ዕቅድ አቅምና ማረጋገጫ ማስረጃ መሠረት ይሆናል፡፡

፪/ ባለፈቃዱ ለማመልከት እና ፈቃድ ለማግኘት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ከተገኘ ለደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የቁጥር ወሰን የለውም፡፡

## ፲፩. ስለመዛግብት እና ሪፖርቶች

የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ባለፈቃድ ፍቃድ የወሰደው ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንም ይሁን ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የሚከተሉትን ለፍቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም ለሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን ማሳወቅ ይኖርበታል፡-

## 9. Issuance of Grade II Geothermal Resources License

1/ A Grade II Geothermal Resources License shall be issued on an exclusive noncompetitive basis for direct use of geothermal resources in accordance with criteria and form determined by the directives.

2/ A Grade II Geothermal Resources License may be granted without the applicant having previously held a Reconnaissance License or Exploration License, as appropriate;

3/ A Grade II Geothermal Resources Licensee requirements of annual measurement and reporting of:

a) flow of steam and/or hot water;

b) temperature into the facility;

c) temperature out of the facility; and

d) additional measurements required by the Licensing Authority depending on the type of facility, the type and quality of the resource, and the terms of any sales contract.

## 10. Determination of License Area and Number of Licenses Held by Licensee

1/ The size and dimensions of the License Area for a Grade II Geothermal Resources License Area shall be determined to the area reasonably necessary for Grade II operations and on the basis of the submitted applicant's proposal resource and justification provided therein.

2/ There are no limitations on the number of Grade II Geothermal Resources Licenses held by a Licensee, so long as the applicant meets the requirements for applying for and holding a License.

## 11. Records and Reports

The holder of a Grade II Geothermal Resources License, whether such License is issued by the Licensing Authority or the concerned State Authority, shall submit to the Licensing Authority and the State Authority:

፩/ በአደጋ ሳቢያ በሰው ላይ የአካል ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከትል አደጋ ከደረሰ ወይም በውሃ ወይም በአየር ጥራት ላይ ጎጂ ውጤት ከተከሰተ ወዲያውኑ ማሳወቅ፤

፪/ ባለፈቃዱ በየዓመቱ ፈቃዱን ከተሰጠበት ቀን በኋላ ባሉት ስልሳ (፷) ቀናት ውስጥ ያለፈውን ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት የሚከተሉትን በማጣቀስ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በክትትል እቅድ እንደተቀመጠው የጂኦተርማል ሀብቱን ክትትል ውጤት፣

ለ) የወጣውንና ጥቅም ላይ የዋለውን ጂኦተርማል ፈሳሽ መጠን፤

ሐ) ከጂኦተርማል ፈሳሹ የወጣ ተረፈ-ምርት ካለ መጠኑን ወይም ከሽያጭ ሥራው የተገኘ ውጤት፤

መ) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች ብዛት፡፡

## ክፍል ሶስት

## ፈቃዶችን ስለማደስ፣ ስለመተካት ፣ ስለማስተላለፍ እና ስለመሰረዝ

### ፲፪. ስለምርመራ ፈቃድ ዕድሳት

፩/ የምርመራ ፈቃድን ለማደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃዱ ዘመን ከመፈፀሙ ከስልሳ (፷) ቀናት በፊት የሚከተሉትን በማሟላት መቅረብ አለበት፡-

ሀ) በፍቃድ ዘመኑ ጊዜ የሚጠበቁበትን ሁሉንም መስፈርቶች ስለማሟላቱ ማስረጃ፣

ለ) ፈቃዱ በመጀመሪያ ሲሰጥ ወይም ዕድሳት ከመከናወኑ በፊት የተደረጉ ለውጦች ካሉ በወቅቱ የቀረቡ መረጃዎች፤

ሐ) በመመሪያ የሚወሰኑ መረጃዎችን ያካተተ ዓመታዊ ሪፖርት፤

መ) በቅርብ ጊዜ ላከናወናቸው የምርመራ ሥራዎች ለሚቀርበው ሪፖርት የሥራ ፕሮግራም እና ለሥራው የወጣ ወጪ፣

ሠ) አመልካቹ በዕድሳት ጊዜው ለመስራት ያቀደው የሥራ ፕሮግራም እና ወጪዎች ዕቅድ፤

1/ inform immediately, any occurrence or accident resulting in or potentially resulting an injury or death to humans or detrimental impacts to water or air quality

2/ the licensee shall submit each year within sixty (60) days after the anniversary of license issuance a report with respect to the previous year considering the following:

a) the results of monitoring of the resource as provided in the Licensee's monitoring plan;

b) the volume of geothermal fluids extracted and used;

c) the quantities of by-products, if any, extracted from geothermal fluids, or products from commercial operations;

d) the number of persons employed, by category.

## CHAPTER THREE

## RENEWAL, SUBSTITUTION, TRANSFER AND REVOCATION OF LICENSE

### 12. Renewal of an Exploration License

1/ An application for the renewal of an Exploration License shall be made at least sixty (60) days before the end of the license term, and shall include the following:

a) evidence that all requirements during the term of the License have been met;

b) any change in the information submitted in applying for the original license or a prior renewal thereof;

c) annual reports containing information as specified by directive;

d) details of the work program that the Licensee has carried out in the most recent period(s) for which a report is due, and related expenditure;

e) plan for the work program and expenditures that the applicant proposes to carry out and incur during the renewal period;

ረ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፈቃደኝነት ከፈቃድ ቦታው ከየትኛው አካባቢ በከፊል የሚለቀው ቦታ ካለ ዝርዝር፣

ሰ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊቀርቡ የሚገባቸውን ሌሎች መረጃዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቀረበውን የዕድሳት ጥያቄ እና ሰነዶች ከመረመረ በኋላ ተገቢው የዕድሳት ክፍያ ሲፈጸምና የዕድሳት ጥያቄው ሲጸድቅ በአዋጁ አንቀጽ ፲፭ (፫) መሠረት በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምርመራ ፈቃዱ ይታደስለታል፡፡

፫/ በመጀመሪያው የምርመራ ፈቃድ ዘመን የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ማረጋገጫ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ካልተጠናቀቀ የምርመራ ፈቃድ ዕድሳቱ አይከናወንም፡፡

## ፲፫. <u>የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ዕድሳት</u>

የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የሚሰጠው ከሀያ አምስት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ በሚቀርበው የፕሮጀክቱ ጥናት ላይ በመመርኮዝ እና የፕሮጀክቱ የፈቃድ ጊዜ ሲያበቃ በመመሪያው እንደሚገለጸው እንደ መጀመሪያው ፈቃድ ተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ መሠረት ሊታደስ ይችላል፡፡

## ፲፬. <u>ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>

፩/ የምርመራ ፈቃድ ወይም በደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ለማስተላለፍ በአዋጁ ፳፮ በተደነገገው መሠረት በጽሁፍ በመመሪያ በሚወጣው የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና በማያያዝ ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም የሚከተሉትን በማካተት መቅረብ አለበት፡-

ሀ) ፈቃዱ ሊተላለፍለት የተፈለገውን ሰው ማንነት፣ የቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም የሚያሳይ መረጃ፣

ለ) ባለፈቃዱ የፍቃድ ቦታውን ሙሉ ለሙሉ ወይም ከአንድ ብሎክ በላይ ከሆነ በከፊል ለማስተላለፍ ስለፈለጋቸው ብሎኮች ማረጋገጫ፣

f) if there is an area to be relinquished, details of any part of the License area to be voluntarily surrendered, subject to the requirements of Article 27 of the Proclamation; and

g) such other information as the Licensing Authority may request to be determined by the directives.

2/ After evaluating the submitted renewal application and documents upon payment of the prescribed renewal fees by the applicant, the Licensing Authority shall renew the Exploration License in accordance with Article 15 (3) of the Proclamation;

3/ License renewal shall not be granted if confirmation of the deep reservoir is not complete within the initial license period.

## 13. <u>Renewal of Grade II Geothermal Resources License</u>

A Grade II Geothermal Resources License shall be issued for a maximum period of 25 years and based on submitted studies on the project may be renewed at the end of the period on substantially the same terms and conditions as the original license, as provided in directives.

## 14. <u>Transfer of License</u>

1/ An application for the transfer of an Exploration License or Grade I Well-field Development and Use License in accordance with Article 26 of the Proclamation shall be made in writing in a prescribed form to be established in directives, with an accompanying fee, and shall include the following:

a) information regarding the identity and technical and financial qualifications of the proposed transferee;

b) certification that the Licensee's interest in the license area will be transferred in its entirety or if it has more than one block part of the blocks;

ሐ) ፈቃዱ ሊተላለፍለት የተፈለገው ሰው የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች እንዲሁም አግባብ ያለው የሥራ ፕሮግራምና ወጪ የባለ ፈቃዱን ሌሎች ግዴታዎች አክብሮ ለመፈጸም ግዴታ መግባቱን የሚያረጋግጥ የተፈረመበት ማስረጃ፣

መ) የታሰበውን ማስተላለፍ የሚመለከቱ የውል፣ የኢኮኖሚና ገንዘብ ነክ ስምምነቶችና ግዴታዎች ዝርዝር፡፡

፪/ የምርመራ ፈቃድ ወይም በደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ በእዳ ለማስያዝ በጽሁፍ በመመሪያ በሚጸድቀው የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና በማያያዝ ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም የሚከተሉትን በማካተት መቅረብ አለበት:-

ሀ) በዕዳ ያዥነት የሚተላለፍለት ሰው ማንነት፣

ለ) ሊሰጥ ስለታቀደው የደህንነት ጥበቃ ሁኔታና አኳኋን፣ እና

ሐ) ፈቃዱን የሚቀበለው የፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የሚጠይቀውን መሟላት የሚገባቸውን ለሟሟላት እና የፍቃዱን ውሎችና ግዴታዎች ለማክበር የሚያስፈልጉትን የገንዘብ እና የቴክኒካል መስፈርቶች ማረጋገጥ፣ የሚገባውን የደህንነት ጥንቃቄ፣ የሥራ ፕሮግራም እና ሌሎች የባለፈቃዱ ግዴታዎች ማሟላት፡፡

፫/ ለደረጃ II ጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የማስተላለፍ ወይም በዕዳ የማስያዝ ማመልከቻ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከተቀበለ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፯ መሠረት የተቀመጡትን አስፈላጊ መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እነዚህን ማመልከቻዎች መገምገምና በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ውሳኔዎችን መስጠት አለበት፡፡

## ፲፭. ስለማገድና ስለመሰረዝ

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፴፫ ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ በአንዱ ማንኛውንም ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል:-

c) a notarized affidavit signed by the proposed transferee agreeing to undertake and comply with all the terms and conditions of the license, including the applicable work program and expenditure and any other undertakings of the Licensee; and

d) all details of the contractual, economic and financial terms and conditions of the proposed transfer or assignment.

2/ An application for the encumbrance of an Exploration License or for Grade I Well-field Development and Use License shall be made in writing on a prescribed form to be established in directives, with an accompanying fee, and shall include the following:

a) information as to the identity of the proposed encumbrancer;

b) the nature, terms and conditions of the security interest proposed to be granted; and

c) the conditions under which the proposed security interest would be realized, including such safeguards as the Licensing Authority may require to assure the financial and technical qualifications of the eventual acquirer of the license and its undertaking to respect the terms and conditions of the license, the work program and any other obligations of the Licensee.

3/ Application for transfer or encumbrance of a Grade II Geothermal Resources License, if the oversight of such License is undertaken by the Licensing Authority, shall meet the applicable requirements of this regulation in accordance with Article 7.

4/ The Licensing Authority shall review such applications and issue decisions as provided in directives.

## 15. Revocation and Suspension

The Licensing Authority may revoke any license on any of the grounds listed under Article 33 of the Proclamation:

፩/ አስቀድሞ በማሳወቅ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አስተዳደሪያዊ ትእዛዞችን በመስጠት ቅጣቶችን ሊወስን ይችላል፤

፪/ የፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕጎች መሠረት ማንኛውንም ተጨማሪ ቅጣቶች ወይም መፍትሄዎችን ሊሰጥ ይችላል፤

፫/ ከፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ውጪ በሆነ በሌላ ባለሥልጣን የተሰጡ ፈቃዶች ሊሰረዙና ሊታገዱ የሚችሉት ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎችና ደንቦች መሠረት ይሆናል፡፡

## ፲፮. የፈቃድ ወረቀት ስለመተካት

ባለፈቃዱ ለጠፋበት ወይም ለተበላሸበት የፈቃድ ወረቀት የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲተካለት መጠየቅ ይችላል፤ ከሚመለከተው የመንግሥት መስሪያ ቤት ማረጋገጫ ተያይዞ ጥያቄ እንደቀረበና ተገቢው ክፍያ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፷፪ መሠረት ሲፈጸም የፈቃዱ የምስክር ወረቀት ምትክ ይሰጠዋል፡፡

## ክፍል አራት

## መረጃ ስለመያዝ ፣የፈቃድ አሰጣጥ እና የፈቃዱ አፈፃፀም ሁኔታ

## ፲፯. የመረጃ አደረጃጀት ስርዓት ዝርጋታ

፩/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦሎጂካል ሀብት መረጃ የመሰብሰብ እና የማደራጀት ሥርዓት ከኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ ከተቋቋመ ተቋም ጋር በመተባበር ይዘረጋል፡፡

፪/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ የተቋቋመ ተቋም ትብብር በሚከተሉት ተግባራትና መርሆዎች ይመራሉ፡-

ሀ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ ከተቋቋመ ተቋም መረጃ ማግኛ፣ ተደራሽነት እና ኃላፊነቶች ጋር የተያያዙ የመግባቢያ ስምምነት ይፈጽማሉ፤

1/ Following notice, the Licensing Authority may issue administrative orders and assess penalties as provided in directives;

2/ The Licensing Authority may pursue any additional sanctions or remedies authorized under the laws of Ethiopia;

3/ Revocation or suspension of Licenses issued by an authority other than the Licensing Authority shall be in accordance with applicable laws and regulations.

## 16. Replacement of License

The Licensee may apply to the Licensing Authority for the replacement of a license document that has been lost or destroyed. Upon receiving such a request with justification from the relevant authority that it has been lost or destroyed, and have paid payment of applicable fees as provided in Article 62 of this Regulation, the Licensing Authority shall issue a replacement of such license to the Licensee.

## PART FOUR

## DATA MANGEMENTE ,CONDITION OF ISSUANCE AND PERFORMANCE OF THE LICENSES

## 17. Establishment of Data Management System

1/ The Licensing Authority shall establish a process for geothermal resources data collection and management in cooperation with GSE or a successor entity responsible for geothermal data acquisition management and accessibility.

2/ Coordination between the Licensing Authority and GSE or its successor entity will be guided by the following actions and principles:

a) The Licensing Authority and Geological Survey of Ethiopia (GSE) or its successor entity shall execute a memorandum of understanding relating to responsibilities for data acquisition management and accessibility;

ለ) ከኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ ከተቋቋመ ተቋም ደረጃውን የጠበቀና ወጥ የሆነ የዳታ ምዝገባ፣ የሪፖርት ፕሮቶኮሎችን የትግበራ መለኪያ እና ለመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበትን ሰው በመሾም የዳታ ተዓማኒነትን እንዲረጋገጥ ያደርጋሉ፤

ሐ) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን መረጃዎች በሚጠየቁበት ጊዜ ተፈጻሚነት ባላቸው ሕግና በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ይሰጣል፤ እንደአግባቡ ተገቢ ክፍያዎችን ሊያስከፍል ይችላል፤

መ) በኢትዮጵያ የጂኦተርማል ሀብት መረጃ የማደራጀት ሥርዓት ከተዘረጋ የመረጃ ቋት በማቋቋም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ክፍል በመመስረት የኢትዮጵያን የጂኦተርማል ሀብት መረጃ ወደ ቋቱ በማስገባት ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ተደራሽ ማድረግ፣

ሠ) የረጅም ጊዜ ግቡ በነባር ወይም በአዲስ የመንግስት አካል የሰው ኃይል እና በመሳሪያ አቅምን በመገንባት፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት በመዘርጋትና በማስተዳደር ሃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ የመረጃውን ምንጭና መረጃውን በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ለህዝብ እና የግል ጠያቂዎች ምላሽ ለመስጠትና መረጃን ለማሰራጨት ማስቻል ነው፡፡

## ፲፰. ስለ ጂኦተርማል ሀብት መዝገብ

፩/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፱ መሠረት ከተገለፁ የሚመዘገቡ የጽሑፍ ሰነዶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የጽሑፍ ሰነዶች በጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ይመዘግባል፡-

ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ ትንበያዎችን የሚያመለክቱ የጂኦተርማል ሀብት ሊገኙባቸው ይችላሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን ሆኖም ያልተረጋገጠባቸውን ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ እና ጂኦግራፊክ ኮርዲኔት፣

ለ) በአዋጁ መሠረት ፈቃድ የተሰጠባቸው ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ፣

ሐ) በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የታደሱ ፈቃዶች ፣ የፈቃድ ቁጥሩንና የቦታውን ስም፣

b) GSE or its successor entity shall ensure data integrity through appointment of a person who is responsible for establishing and overseeing implementation of standardized, consistent data recording and reporting protocols;

c) The Licensing Authority shall provide information upon request according to applicable law and directives and may charge reasonable fees as appropriate;

d) Upon establishment of the process and repository for geothermal resources data, electronic data rooms shall be developed containing information about geothermal resources in Ethiopia, and a process for access to those data rooms by the general public shall be established in directives;

e) The long-term goal is to build capacity in an existing or new government entity that is responsible for establishing and managing electronic databases, with metadata to identify the source of data, and dissemination of data in response to public- and private-sector requests.

## 18. Establishment of Register of Geothermal Resources;

1/ In addition to the listed documents as provided in Article 9 of the Proclamation, the Licensing Authority shall establish and maintain a Register of Geothermal Resources documents with the following information :

a) Maps and geographic coordinates providing a general representation of areas where preliminary analysis indicates geothermal resources may be available but have not been confirmed;

b) maps showing areas issued licenses under the Proclamation;

c) licenses renewed under the Proclamation and this Regulation , their license numbers and locations;

መ) ፈቃድን፣ የፈቃድ መብትን፣ የፈቃድ ቦታን ወይንም የተወሰነውን የፈቃድ ቦታ የማስተላለፍን፣ የጊዜ ማራዘምን፣የመተውን፣ የመሰረዝን ወይም የማቋረጥን፣ማስታወቂያ ዎችን እና/ወይም ትዕዛዞችን፣ እና

ሠ) በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ቦታዎችን የሚያሳይ ካርታና ጂኦግራፊክ ኮርዲኔቶችን፡፡

፪/ እያንዳንዱ ማመልከቻ ለፈቃድ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፣ በተጨማሪም በጨረታ ጊዜ ስኬታማ ተጫራች አመልካች በሚፈርምበት ጊዜ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## ፲፱. የጂኦተርማል ስራ ፈቃድ ማመልከቻዎችን ስለማረጋገጥ እና ምዝገባ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ ደንብ መሠረት የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻው በደረሰው (፫) በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ መስፈርቱን የሚያሟላ መሆን እና አለመሆኑን በማጣራት ይወስናል፣ ማመልከቻው መስፈርቶቹን አሟልቶ ካልተገኘ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ለአመልካቹ ማመልከቻው ተቀባይነት አለማግኘቱን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻው ሁሉንም መስፈርቶች እንዳሟላ ካረጋገጠ ወዲያውኑ በመመዝገብ ለአመልካቹ ስለምዝገባው በጽሁፍ የምዝገባውን ቀን በመጥቀስ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፳. የጂኦተርማል ስራ ፈቃድ ማመልከቻዎችን ስለማስታወቅ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ (፪) መሠረት የሕዝብ ማስታወቂያው ወጥቶ ሰላሳ ቀናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምርመራ ፈቃዱን ለመስጠት ማመልከቻ ያቀረቡ አመልካቾችን ሰነዶች በ አስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የቴክኒካልና የገንዘብ አቅም መስፈርት መሠረት በመገምገም ከሁሉም አመልካቾች የሚበልጠውን ይወስናል::

፪/ የሕዝብ ማስታወቂያው በወጣበት ሰላሳ ቀናት ውስጥ ሌላ ማመልከቻ ካልቀረበ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለአመልካቹ የምርመራ ፈቃዱን ለመስጠት የቴክኒክና የገንዘብ አቅም መስፈርቱን ያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ሰነዶቹን በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ይገመግማል::

d) notices and/or orders of transfer, extensions, surrender, termination and revocation of licenses and license areas, or portions of license areas; and

e) GPS coordinates and maps of Known Geothermal Resources Areas, as such designation may be provided in directives.

2/ Upon receipt of an application, including an application signed by a successful bidder following bid award, the Licensing Authority shall be registered.

## 19. Geothermal Applications Verification and Registration

1/ Within 3 working days of receipt of the geothermal operations application, the Licensing Authority shall review an application to determine whether it meets the requirements for completeness as provided in this regulation and/or directive. If the application has not satisfied the requirements, it will be rejected and the Licensing Authority shall give a written notification to the applicant its reason.

2/ If the Licensing Authority determines that the application fulfills all the requirements, it shall promptly register such application and shall notify the applicant of such registration in writing, indicating the date thereof.

## 20. Geothermal Operations License Applications Notice

1/ In accordance to the proclamation Article 17 (2), after the 30 days of publication period expired, the Licensing Authority shall evaluate within 15 days all applications documents submitted to determine the best application from all applicant based on technical and financial criteria for the award of the application;

2/ If there are no additional application received during the 30 days publication period, the Licensing Authority shall evaluate the technical documents and financial capacity of the original applicant within 10 working days to determine the suitability of the application for the exploration license request;

፫/ የቴክኒካልና የገንዘብ አቅም መስፈርት በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ይወጣል፡፡

፬/ ከምርመራ ፈቃዱ ግምገማ እና የቅኝት፣ ደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ወይም ደረጃ II ጂኦተርማል ሀብት የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ከተመዘገበ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ ፲ መሠረት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፍቃዱ የሚገኝበትን ቦታ እና ስለ ፕሮጀክቱ ማብራሪያ በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት ማስታወቂያ በማዘጋጀት ለፈቃድ ጠያቂው በመስጠት በአገሪቱ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ እንዲወጣ በማድረግ ለአስራ አምስት ቀናት እንዲቆይ ማድረግ አለበት፡፡

፭/ አመልካቹ በዚህ ደንብ በሚወጣ መመሪያ መሠረት ሁሉንም ለምዝገባውና ለህትመት የሚወጣውን ወጪዎች መሸፈን አለበት፡፡

## ፳፩. የፍቃድ መስፈርቶች እና ግዴታዎች

የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የቀረበውን ማመልከቻ በመገምገም በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና በሚወሰን መመሪያ መሠረት ተሟልተው ሲገኙ በሚከተሉት መጠይቆች እና መስፈርቶች መሠረት ፈቃድ መስጠት አለበት፡

፩/ ለምርመራ ፈቃድ፡-

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፲፭ እና አንቀጽ ፲፯ (፪) በተደነገገው መሠረት የብቻ የሆነ መብት ቶሚያስገኝ ፈቃድ በውድድር በመመሪያ በሚወሰነው ቅጽና መስፈርት መሠረት ይሰጣል፤

ለ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በምርመራ ፈቃድ መሥፈርት መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ ባለፈቃዱ የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ የእያንዳንዱ ፈቃድ ቦታ ከሃምሳ (፶) ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የምርመራ ፈቃድ ቦታውን በአጠቃላይ ወይም በከፊል በሚሸፍን ቦታ ለማግኘት መብት ይኖረዋል፣ ሆኖም የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ለማግኘት በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና በሚወጣ መመሪያ መሠረት መስፈርቶችና ግዴታዎች የምርመራ ፈቃድ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡

3/ The technical and financial criteria shall be set out in directives issued hereunder.

4/ Following the evaluation for the exploration license, and registration of each application for Reconnaissance, Grade I Well-field Development and Use or Grade II Geothermal Resources license, the Licensing Authority shall prepare a notice setting out the location and description of the proposed project and other details as may be established in directives, and shall provide the text of such notice to the applicant for publishing in accordance to Article 10 of the Proclamation.

5/ The applicant shall pay all costs for registrations and publications required under this Regulation, as provided in Directives.

## 21. Terms and Conditions of Licenses

The Licensing Authority shall review an application and upon a determination that the requirements of the Proclamation, this Regulation and Directives have been met, issue a license upon the following terms and conditions:

1/ An Exploration License:

a) may be issued on an exclusive and competitive basis, as provided in Article 15 and Article 17 (2) of the Proclamation, and in a form and with conditions as set forth in directives;

b) the Licensing Authority when granting an Exploration License, on such conditions as the Licensing Authority may determine and set out for the Exploration License, the licensee has the right to be issued one or more Grade I Well-field Development and Use License for all or part of the area covered by the Exploration license which each area may not exceed fifty (50) square kilometers, provided that the Exploration Licensee applies meets the requirements for issuance of such license as set forth in the Proclamation, this regulation and directives issued hear under , and this Exploration Licensee has fulfilled the work program requirements established in

፪/ ለምርመራ ፈቃድ ወይም የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ፡-

ሀ) አግድም የሚቆፈሩ ጉድጓዶችን ጨምሮ በፈቃድ ክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ ማናቸውም የጂኦተርማል ሥራዎች አዋሳኝ የሆኑ የሌሎች የጂኦተርማል ፈቃዶች ክልል ውስጥ ጣልቃ መግባት የለባቸውም፤

ለ) ለእያንዳንዱ ጉድጓድ ወይም አንድ የጉድጓድ አፍ ለሚጋሩ ጉድጓዶች የጂኦተርማል ፈሳሹን ፍሰት፣ ሙቀትና የግፊት ልኬት መጠን በአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የአሰራር ኮድ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ባገናዘበ መልኩ መለካትና ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሪፖርት ማድረግ፣

ሐ) የኤሌክትሪክ ማመንጨያ መሣሪያዎች የሚከተሉትን ጨምሮ መለካትና በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት መደረግ አለበት፡-

(፩) ወደ ማመንጫ ተቋሙ የሚገባው የእንፋሎት ወይም/እና ሙቅ ውሃ መጠን፤

(፪) የእንፋሎት ኬሚስትሪ እንደ ክሎራይድ ፣ ፒ.ኤች፣ እርጥበት ወይም የውሃ ኬሚስትሪ፤

(፫) ወደ ማመንጫ ተቋሙ የሚገባው የውሃ እና/ወይም እንፋሎት ሙቀት መጠን፤

(፬) ወደ ማመንጫ ተቋሙ የሚገባው የውሃ እና/ወይም እንፋሎት ግፊት መጠን፤

(፭) አጠቃላይ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል፤

(፮) ማመንጫ ተቋሙ የሚያወጣው የተጣራ ኤሌክትሪክ ኃይል፤

(፯) በመሸጫ ቦታ ላይ የሚቀርብ ኤሌክትሪክ ኃይል፤

(፰) በየዓመቱ ከማመንጫ ተቋሙ የሚወጣው የማይዘቀጥ እንደ ካርቦን ዳዮክሳይድ፣ ሃይድሮጅን ሰልፋይድ፣ ሜቴንና የመሳሰሉ ግምታዊ የጋዝ መጠን፤

(፱) ከማመንጫ ተቋሙ የሚወጣው የእንፋሎት እና/ወይም ሙቅ ውሃ ሙቀት መጠን፡፡

the Exploration License within its period of validity.

2/ An Exploration License or Grade I Well-field Development and Use License:

a) shall include a requirement that geothermal operations may not be undertaken in such a way, including directional surveys of all wells, that create a risk of interference or overlapping of License Areas;

b) shall include, for all well operations, measurement and reporting of wellhead flow, wellhead temperature, and wellhead pressure information, reported at a minimum on an annual basis for each well or shared well header with directives to be issued in accordance with the African Union Code of Practice for Geothermal Drilling;

c) for all electrical generation facilities, measurement and quarterly reporting of:

(1) steam and/or hot water flow into the facility;

(2) steam chemistry (Chloride, pH, wetness) or water chemistry;

(3) temperature of the water and/or steam into the facility;

(4) pressure of the water and/or steam into the facility;

(5) gross electricity generated;

(6) net electricity generated at the facility;

(7) electricity delivered to the sales point;

(8) estimated amount of non-condensable gases ($CO_2$, $H_2S$, and $CH_4$) vented by the plant on an annual basis; and

(9) temperature of the steam and/or hot water exiting from the facility.

፫/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው፡-

ሀ) የብቻ የሆነ መብት ያለው፣ የምርመራ ፈቃድ በውድድር አሸንፎ ፈቃድ የተሰጠውና የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ለማግኘት የተቀመጡትን ሁኔታዎች ያሟላ፣ ወይንም በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ (፩) እና በዚህ ደንብ የተደነገገውን በውድድር ፈቃድ የማግኘት መብት አሟልቶ ሲገኝ፣

ለ) የፀደቀ የኃይል ግዥ ስምምነት ተያይዞ ከቀረበ፣

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ ፳ መሠረት የሚከተሉትን ጨምሮ የያዘ የጸደቀ የሥራ ፕሮግራም ሲቀርብ፡-

(፩) የኃይል ማመንጨት አቅሙ ጋር የአመልካቹን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ የቴክኒክ ሪፖርት፣

(፪) የሚጠበቅ የኃይል ማመንጨት አቅም እና ሌሎች ውጤቶች ወይም ተረፈ ምርቶች፣

(፫) በፈቃዱ ጊዜ የሚጠናቀቁ ሥራዎችን ያካተተ የሥራ አተገባበር ዕቅድ፣

(፬) የጤና እና የደህንነት ዕቅድ፣

(፭) ኃይል ለማመንጨት ወይንም የመነጨውን ኃይል ግዥ አስመልክቶ ከመንግሥት ጋር የተደረጉ ውለታዎችና ስምምነቶች በሙሉ፣

(፮) በባለፈቃዱ የጂኦተርማል ፈሳሹን ለሌላ ጥቅም ለማዋል የተያዘ ዕቅድ ወይንም የጂኦተርማል ፈሳሹን ለሶስተኛ ወገን እንዲጠቀም የተደረገ ስምምነት ዕቅድ ዝርዝር ማብራሪያ፣

(፯) የመረጃ አሰባሰብና አጠባበቅ ዕቅድና ሪፖርት አደራረግን አስመልክቶ ከአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የትግበራ ኮድ ጋር የሚጣጣም በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የሚወጣ ዝቅተኛ መስፈርት እና ሪፖርት አደራረግ የተመለከተ የጊዜ ሰሌዳ ዕቅድ፣

(፰) በፈቃድ ቦታው አካባቢ ከሚገኙ ማህበረሰቦች ጋር በጋራ ተባብሮ ለመስራት የተቀረፀ ዕቅድ፣

3/ A Grade I Well-field Development and Use License shall be granted:-

a) applicant who has exclusive right, that has competitively won the right to an Exploration License and has fulfilled the conditions precedent to Grade I Well-field Development and Use license; or fulfill a competitive process provided in Article 17 (1) of the Proclamation and of this Regulation;

b) shall be accompanied by a valid power purchase agreement;

c) As stated in the Article 20 of the Proclamation, provide an approved work program which include the following:

(1) a technical report on the production possibilities and the intention of the applicant in relation thereto;

(2) expected production capacity for power generation and other output or byproducts;

(3) plan of operations including work to be completed during the term of the License;

(4) health and safety plan;

(5) proposed details of all contracts or arrangements with the government of Ethiopia for development and/or purchase of power generated;

(6) plan for use of geothermal fluids for other purposes by the Licensee or proposed details of arrangements for use of geothermal fluids by third parties, if any.

(7) plan for collecting and reporting data consistent with the African Union Code of Practice for Geothermal Drilling minimum data recording and reporting requirements as provided in directives, and a schedule for reporting,

(8) plan for coordinating to work with communities in the license area;

(፱) ፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ሊያደርስ በሚችልባቸው ማህበረሰቦች ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል ያለው ዕቅድ፣

(፲) በተሰጠው ፈቃድ ሥራ ላይ በከፍተኛ ደረጃ በአካባቢው ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጥፋት ማብራሪያ እና ጥፋቱን ለመቆጣጠር ወይም ለመቀነስ የሚወሰደው እርምጃ ዕቅድ፣

(፲፩) ለአካባቢ ጥበቃ የሚውል ፈንድ ስለማቋቋምና ስለመጠቀም የተዘጋጀ ዕቅድ፣

(፲፪) በፈቃድ ዘመኑ የሚያስፈልግ የካፒታል ኢንቨስትመንት፣ የመደበኛ ሥራ ወጪ እና የገንዘብ ምንጭ የሚያሳይ በጀትና ዕቅድ፣

(፲፫) የጂኦተርማል ሥራውን በሚያከናውን-በት ወቅት ለመቅጠርና ለማሰልጠን የያዘው ዕቅድ፣

(፲፬) የጂኦተርማል ሥራው ሲዘጋ የሚዘጋበት እቅድና በተጨማሪም የማይሰሩ ጉድጓዶችን የመተውና መዝጋት፣ የሚሰሩ ጉድጓዶችን የመክደን እና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚፈቅደው መሠረት ይዞ የማቆየትና የማዘግየት እና የፕሮጀክቱ መሠረተ ልማትና አገልግሎት መስጫ ዕቃዎችን የማስወገድ ሥራ፣

(፲፭) በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንደአስፈላጊነቱ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች ድንጋጌዎች፡፡

መ) ባለፈቃዶች በታቀደው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ስለተከናወኑ ሥራዎች ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ እና የሚቀጥለው ዓመት የሥራ ዕቅድ እና ወጪ በመመሪያ በሚደነገገው መሠረት ማቅረብ አለባቸው፡፡

## ፳፪. የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና የማመንጨት ፈቃድ ግንኙነት

በመጀመሪያ ለሚገነባው የኃይል ማመንጫ ተቋም እና በመቀጠል በፈቃድ ቦታው በተጨማሪ ለሚገነቡት ለእያንዳንዱ የኃይል ማመንጫ ተቋሞች የማመንጨት ፈቃድ ለደረጃ I

(9) plan for minimizing or mitigating the impacts of the project on affected communities;

(10) a statement of any significant adverse effect which the carrying out of operations authorized under the license would be likely to have on the environment and a plan for controlling or mitigating that effect;

(11) plan for establishment and use of an environmental fund;

(12) a detailed budget and financial plan showing capital investment; operating costs and source of financing during the term of the license;

(13) plan to employing and training during the time of the geothermal operations under the license;

(14) plan for closure including plugging and abandonment of unserviceable wells; capping of serviceable wells and retention for future use as may be authorized by the Licensing Authority; and removal of project infrastructure and facilities; and

(15) any additional terms and conditions as stated in directives to be issued hereunder by the Licensing Authority.

d) Licensees shall be required to submit an annual report describing progress in implementing the work program, and tasks and expenditures as well as plans for the next/subsequent year as set forth in directives.

## 22. Relationship of Grade I Well-field Development and Use License and Power Generation License

For the initial power plant and for each additional power plant built within the License Area, a power generation license shall be issued during the term of the Development and Use

የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ያህል ጊዜ ይሰጣል፡ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጫ ፈቃድ ሲፈቀድ እንዲህ ዓይነቱን ፈቃድ ከሚመለከተው የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ጋር በማጣቀሻነት በማያያዝ ይካተታል፡፡

License, upon issuance of a power generation license such license shall be incorporated into the Grade I Well-field Development and Use License by reference.

## ፳፫. <u>በባለፈቃዶች መያዝ የሚቻለው የፈቃድ ቁጥር ብዛት እና የፈቃድ ቦታ ስፋት ወሰን</u>

የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

፩/ የቅኝት ባለፈቃድ በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ፈቃዶችን መያዝ ቢችልም የእነዚህ ፈቃዶች ጠቅላላ ስፋታቸው ከሁለት ሺህ (፪ሺ.) ካሬ ኪሎ ሜትር መብለጥ አይችልም፡፡

፪/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ በፈቃዱ የተቀመጡትን ግዴታዎች ከተገበረ እና በሥራ ፕሮግራሙ የተቀመጡትን ካከበረ፡ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ የፈቃድ ብዛት ቁጥር ወሰን የለውም፡፡

## 23. <u>Determination of License Area and Number of Licenses held by Licensees.</u>

Without prejudice to the provisions of Article 23 of the Proclamation:

1/ For a Reconnaissance License at any point in time a Licensee may hold multiple Reconnaissance Licenses, provided that the total area held by the Licensee under all such licenses may not exceed two thousand (2,000) square kilometers.

2/ For a Grade I Well-field Development and Use License there are no limitations on the number of Geothermal Well-field Development and Use Licenses held by a Licensee, so long as the applicant meets the requirements for a License, and, if already a Licensee, is in compliance with its work program and terms of its License(s).

## ፳፬. <u>የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና በተጨማሪ የተጣመረ የኃይልና ሙቀት በጋራ ስለመጠቀም</u>

፩/ የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ አመልካች ወይም ባለፈቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ተረፈ-ምርት ፍሳሹን በምን መልኩ ለመጠቀም እንዳቀደ የሚያሳይ የሥራ ፕሮግራም ማቅረብ ይችላል፡ በተጨማሪም፡-

ሀ) ለታቀደው ጥቅም ማብራሪያ ዕቅድ፡

ለ) ኤሌክትሪክ ከማመንጨት በተጨማሪነት ከጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ምንጩ ለመጠቀም የታቀዱት ሥራዎችና በምንጩ ላይ ሊኖረው ይችላል ተብሎ የሚታሰበው ተጽእኖ ፡ እና

ሐ) የጥምር ሥራው በሠራተኞች፡ በጤናና በደህንነት ጥበቃ፡ የማህበረሰብ ልማትና የባለፈቃዱ የፋይናንስና ቴክኒካል አቅም፡ የበጀት፡የአካባቢ ጥበቃ፡ ኢኮኖሚ እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ተብለው በመመሪያ የሚወሰኑ ሁኔታዎችላይ ያለው ተፅዕኖ፡፡

## 24. <u>Grade I Well-field Development and Use License including Combined Power and Heat</u>

1/ A Grade I Well-field Development and Use applicant or Licensee may submit documentation as part of the work program to the Licensing Authority describing the proposed use of used geothermal fluids, as appropriate including:

a) a description of planned additional use(s);

b) plan to use from the source reservoir in addition to electric generation and the anticipated effects on the source; and

c) the combined operations as they may affect employees, health and safety, community developmentfinancial and technical capability of the Licensee, budget, the environment, economy, and other considerations as may be established in directives.

፪/ ለአዲስ የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ አመልካች፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመስፈርቱ መሠረት ተሟልቷል ብሎ ሲያምን እና የአመልካቹ የኃይልና የሙቀት የጋራ የመጠቀም ጥያቄ ዕቅድ እንዲሁም በጀት በህዝቡ ደህንነትና በጂኦተርማል ሀብቱ ላይ ተፅዕኖ እንደሌለው ሲያምን የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና የጂኦተርማል ፈሳሽን ለኃይልና ለሙቀት የመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፫/ ቀደም ሲል የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ የጂኦተርማል ፈሳሹን ለተጨማሪ ጥቅም ለማዋል የቀረበው ዕቅድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ሲያገኝና ተገቢው ክፍያ ሲፈጸም እንዲሁም ባለው ፈቃድ ኃይል በማመንጨት ላይ ምንም ተፅዕኖ ከሌለው፣ ባለፈቃዱ በግልጽ የቴክኒክ ወይም የገንዘብ ችግር እንዳለበት ካልታየ በስተቀር ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሻሻለ የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና የጂኦተርማል ፈሳሽ ኃይልና ሙቀት በጋራ የመጠቀም ፈቃድ ላለው ፈቃድ ዘመን ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፳፭. ዝቅተኛ የሥራ እና የማሻሻያ መስፈርቶች

፩/ ለቅኝት ፈቃድ በፈቃዱ ዘመን መጨረሻ የተጠናቀቁ ሥራዎች የማጠቃለያ ሪፖርት እና ያልተጠናቀረ ጥሬ መረጃ እና የተጠናቀረ መረጃ መቅረብ አለበት፡፡

፪ ለምርመራ ፈቃድ፡-

ሀ) ባለፈቃዱ በየዓመቱ የተከናወኑ ሥራዎች ማጠቃለያ ሪፖርት እና የተሰበሰበ ያልተጠናቀረ ጥሬ መረጃ እና የተጠናቀረ መረጃ፣ የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ ዕቅድ እንዲሁም ወጪና በቂ ምክንያት የያዘ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፣

ለ) ባለፈቃዱ በሶስተኛ ዓመት መጨረሻ ወይም ከዚያ በፊት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የመጀመሪያ የቅድመ ፅንሰ ሃሳብ ሞዴልና ማብራሪያ፣ ስለ ጂኦተርማል ሀብት ከመሬት ገጽታ ምርመራ ሥራና ከጉድጓድ ቁፋሮ ምርመራ ዕቅድ በመነሳት ማቅረብ አለበት፣

2/ For new Grade I Well-field Development and Use applications, if the Licensing Authority is satisfied that the applicant has met the requirements for a license, and that the applicant's plan for the combined use, including budget, is well founded and will not be detrimental to the public welfare and conservation of the resource, it shall issue a Grade I Well-field Development and Use license that includes authorization to use geothermal fluids for Combined Power and Heat purposes.

3/ For existing Grade I Well-field Development and Use Licenses, upon review of the Licensee's proposal and receipt of the required fees, if the Licensing Authority is satisfied that the additional use of the geothermal fluid does not have a negative impact on the power generation of the existing license, and unless there is a clear evidence that the Licensee does not have the technical or financial capability to undertake the additional operations and use of the resource, the Licensing Authority may issue an amended Grade I Well-field Development and Use License authorizing the use of geothermal fluids for Combined Power and Heat purposes, provided however that such an amendment has no effect on the duration of the License period.

## 25. Minimum Work and Updates Requirements

1/ For a Reconnaissance License at the end of license term, a report having summary of the work completed and submittal of the raw data gathered and its interpretation.

2/ For an Exploration License:

a) annually, the Licensee shall prepare a report including a summary of the work completed, and submittal of the raw data gathered and its interpretation, and planned adjustments to the work program, including costs, with justifications.

b) at or before the end of the third year, the Licensee shall submit to the Licensing Authority a preliminary conceptual model and description of resource characteristics based on surface exploration and drilling plan.

ሐ) ባለፈቃዱ በአራት ዓመት መጨረሻ ወይም ከዚያ በፊት የጂኦተርማል ምርት ማረጋገጫ የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መጀመር አለበት፡፡

፫/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ፡-

ሀ) የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ በተሰጠ በአራት ዓመት ውስጥ ባለፈቃዱ ኤሌክትሪክ የማመንጨት ፈቃድ የመጠየቅ መብትና ኃላፊነት አለበት፣

ለ) የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ከተጀመረ በአራት ዓመት ውስጥ ባለፈቃዱ ከጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ልማት ሥራ ጋር በተያያዘ እንደ ምርት እና ሪኢንጀክሽን ጉድጓድ ቁፋሮ እና ሌሎች ሥራዎች ማከናወን ይገባዋል፡ የተሻሻለ የፅንሰ ሃሳብ ሞዴልና ማከማቻ ሪፖርት፣ የምርት እና የሪኢንጀክሽን ጉድጓድ ቁፋሮ ሊያከናውን የሚችልባቸው ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ ዕቅድ እና በቀሪው ፈቃድ ዘመን የሚገነቡ አገልግሎት መስጫዎች ዕቅድ ማቅረብ አለበት፣

ሐ) ባለፈቃዱ በየዓመቱ መጨረሻ ባሉ ስልሳ ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ዝቅተኛውን መረጃ ማስረከቢያ መስፈርቶች እንደ የምርት እና ሪኢንጀክሽን መረጃዎች በመመሪያ በሚወጣው መሠረት እና ማሻሻያ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ማቅረብ አለበት፡፡

## ፳፮. ስለመዛግብት እና ሪፖርት

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ የሚከተሉትን የያዘና በእነዚህ ላይ የሚደረጉ ወቅታዊ ለውጦችን የሚያሳይ መዝገብ በኢትዮጵያ ውስጥ መያዝ አለበት፡፡

ሀ) መደበኛ መዛግብት፡-

(፩) የሰውን ጤንነት ወይም አካባቢን የሚጎዱ ወይም ጉዳት የሚያደርሱ አደጋዎች ወይም ግጭቶችን መመዝገብና በተፈጸመ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ሪፖርት ማድረግ፣

(፪) በሥራ እና በአገልግሎት ላይ የተደረገ ለውጥ ካለ፣

(፫) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች መረጃዎች፣

c) at or before the end of the fourth year, the Licensee shall commence drilling of deep reservoir confirmation wells.

3/ For a Grade I Well-field Development and Use License:

a) within four (4) years of issuance of a Grade I Well-field Development and Use License the Licensee shall have the right and responsibility to apply for a power generation license;

b) within four (4) years of the start of the Grade I Well-field Development and Use License, the Licensee shall conduct the activities related to the development of the geothermal reservoir like drilling of production and reinjection wells and other site activities; submit a refined conceptual model and reservoir report, and a site plan showing probable future production and reinjection well locations, plant location, and other facilities to be constructed in the remaining license period;

c) within sixty (60) days of the end of a year, the Licensee must meet minimum data handover requirements (such as production and reinjection data) as required in directives to be issued and an updated work program and budget.

## 26. Records and Reports

1/ Any licensee shall maintain records in Ethiopia during the term of the license and current changes with regards to these records as follows:

a) regular records of:

(1) register accidents or incidents that endanger or harm human health or the environment, and shall report the same with in 24 h'rs after the event;

(2) changes to facilities and operations;

(3) the number of persons employed, by category;

(፬) የሁሉም መሳሪያዎች፣ ማሽኖች እና ሌሎች ቁሳዊ ንብረቶች ዝርዝር፡፡

ለ) ሁሉንም የቴክኒካል ሪፖርት ትንተና፣ ከአካባቢ ጥበቃ እና ከፍቃድ ቦታው የጂኦተርማል ሀብት ጋር የተያያዙ ሪፖርቶች ቅጂዎች፡፡

ሐ) በሥራ ፕሮግራሙ በታቀደው መሠረት እና ለቁፋሮ ሥራ በአፍሪካ ሀብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ ትግበራ ኮድ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎች ባከበረ መልኩ በተሰጠው የፈቃድ ቦታ ላይ የተሰበሰበ መረጃ፡፡

፪/ የምርመራ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን መዛግብት መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) በጉድጓድ ቁፋሮ ላይ የተሟላ መረጃና የጉድጓዱ ሎግ መረጃ፣

ለ) የጉድጓዶች በምርት እና በሪኢንጄክሽን ጊዜ የየቀኑን የሙቀት፣ ግፊት እና የጂኦተርማል ፍሰት ሙሉ መረጃ፣እና

ሐ) በፈቃዱ ላይ የተገለጹ ሌሎች መረጃዎች፡፡

፫/ የምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች በመመዝገብ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማስረከብ ይኖርበታል፡-

ሀ) ለእያንዳንዱ ጉደጓድ እና የፍተሻ ሥራዎች ለሁሉም ጉድጓዶች ወርሃዊ ሪፖርቶች፣ ከሎግ ጋር የተያያዘ መረጃ እና ከጉድጓዱ ጋር የተያያዙ የምዝገባ ማስታወሻዎች፣ የቁፋሮና የሙከራ ስራ ውጤቶችን እንዲሁም የጉድጓዱን ማጠናቀቂያ ሪፖርት ያካተተ፣

ለ) የምርመራ ባለፈቃድ በየዓመቱ ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን በኋላ ባሉት ስልሳ ቀናት ውስጥ ያለፈውን ዓመት ማጠቃለያ ሪፖርት የሚከተሉትን የያዘ በዓመቱ ያቀርባል፡-

(፩) በሥራው መርሃ ግብር መሠረት የተከናወነውን ሥራ፣

(፪) የተገኙ ውጤቶች፣

(፫) አደጋዎች ወይም ፍሳሾችን ያካተተ ዋና ዋና የሆኑ ክስተቶች፣

(፬) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች ብዛት፣

(፭) ወጪዎች በየመደብ ዓይነት፡፡

(4) inventories of all equipment, machinery and other physical assets.

b) copies of all technical repot analyses and other reports relating to the environment and geothermal resources in the license area;

c) records of data required to be collected as provided in the License, based on the work program elements and, for drilling, directives issued in compliance with the African Union Code of Practice for Geothermal Drilling.

2/ The Holder of an Exploration License shall record:

a) detailed data on drilling well, including well logs;

b) detailed data on temperature, pressures and flows recorded on a daily basis for periods when wells are in production or reinjection; and

c) other informations as provided in the License.

3/ The holder of an Exploration License shall record and submit the following to the Licensing Authority:

a) For every well and testing operations a monthly report including datas related to logs and information registered related to the well, drilling and test results as well as well completion report

b) once a year, within sixty (60) days after the anniversary of the issuance of the license, a report with respect to the previous year, specifying:

(1) the progress of operations pursuant to the work program,

(2) the results obtained;

(3) events of significance, including accidents or spills;

(4) the number of persons employed, by category; and

(5) expenditures by type.

፬/ የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ባለፈቃድ ፈቃዱን ከወሰደበት ማብቂያ በኋላ ባሉት ስልሳ (፷) ቀናት ውስጥ ያለፈውን ዓመት በየወሩ የተከናወኑትን የሚከተሉትን የያዘ ሪፖርት ያቀርባል፡-

ሀ) አጠቃላይ የወጣው ጂኦተርማል ፍሰት መጠን እና ማንኛውም ከዚያ በኋላ የተከሰተውን ፊዚካላዊ እና ኬሚካላዊ ባህሪያት ያካተተ፤

ለ) ወደ አገልግሎት መስጫው የገባውን የጂኦተርማል ፈሳሽ መጠን፤

ሐ) ከጂኦተርማል ፍሳሽ የወጡ ተረፈ ምርቶች ካሉ መጠናቸው፤

መ) ከፍተኛ ጉዳት ወይንም ሞት ያደረሱ ሁሉንም ክስተቶች እና አደጋዎች ወይንም በማህበረሰቡና በአካባቢው ላይ የደረሱ ተፅዕኖዎች እንዲሁም ተፅዕኖውን ለመቀነስ የተወሰዱ እርምጃዎች፤

ሠ) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች ብዛት፡፡

፭/ የኤሌክትሪክ የመጨረሻ ማስተላለፊያ ቦታ ወይም ባስ ባር ወይም ስምምነት ከተደረገበት ማስተላለፊያ ቦታ ወደ ማስተላለፊያ ግሪድ የተላለፈው የኤሌክትሪክ ኃይል መጠን፡፡

፮/ የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ ቢያንስ በየአምስት ዓመት ውስጥ በፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተቀባይነት ያለው የአሃዝ ሪዘርቮር ሞዴል ጨምሮ ወቅታዊ የጂኦተርማል ፈሳሽ ክምችት ሪፖርት ለፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

፯/ የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ወይም የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ በሕግ ሰውነት ያገኘ ባለፈቃድ፣ ባለፈቃዱ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔውን ባደረገ በዛው ወር ውስጥ የቦርዱን ሪፖርት እና የሂሳብ ተቆጣጣሪዎች ከባለፈው የበጀት ዓመት ጋር የተያያዙ የሒሳብ መግለጫዎች እና በስብሰባው ተቀባይነት ያገኙ ካሉ የጂኦተርማል ልማት ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቅጂዎች ለፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

4/ The holder of a Grade I Geothermal Well-field Development and Use license shall submit to the Licensing Authority each year within sixty (60) days after the anniversary of license issuance a report specifying for each month in the previous year:

a) the total quantities of geothermal fluids extracted and any subsequent variations of their physical and chemical characteristics;

b) the specific quantities of geothermal fluids delivered to the facility;

c) the quantities of by-products, if any, extracted from geothermal fluids;

d) all occurrences and accidents resulting in serious injury or death or impacts to the community or the environment, and steps taken to mitigate impacts;

e) the number of persons employed, by category.

5/ the amount of electricity transmitted from a busbar or other agreed point of delivery to the transmission grid.

6/ The holder of a Grade I Well-field Development and Use license shall submit to the Licensing Authority at least every five years an updated reservoir report including numerical model that is acceptable to the Licensing Authority.

7/ Where a holder of a Grade I Well-field Development and Use license or a Grade II Geothermal Resources License is a juridical person, the holder shall submit to the Licensing Authority, within the month following every annual general meeting, the report of the Board and that of the Auditors, the complete statement of accounts relating to the last financial year, and copies of resolutions relating to geothermal development and operations, if any, adopted at the meeting.

## ክፍል አምስት
## ጨረታ

### ፳፯. ስለ ጨረታ ውድድር

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ እና በዚህ ደንብ መሠረት የምርመራ ፈቃድ እና የደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃዶችን በጨረታ አወዳድሮ ሊሰጥ ይችላል።

### ፳፰. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ኃላፊነት እና ስልጣን

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን አንድን የፍቃድ ቦታ በጨረታ በሚያወዳድርበት ጊዜ የሚከተሉትን መስፈርቶች መከተል ይኖርበታል ፦

፩/ ለጨረታ ማስታወቂያና ለምርጫ ሂደት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፣

፪/ ለጨረታ የሚቀርበውን ቦታ መወሰን፣

፫/ በጨረታ ሰነድ ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ዝቅተኛ የቴክኒክ ብቃትን እና የግንዘብ አቅምን መወሰን፣

፬/ የጨረታውን ምዘና ሂደት ማለትም የኃይል ማመንጫ ተቋማትን ማቋቋም የኤሌክትሪክ ማመንጫ እና የሀይል ፍጆታ ታሪፍን በተመለከተ በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮ አንቀጽ ፬(፫) መሠረት ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር በተያያዘ የሚቀርብለትን ታሪፍ መገምገምና ለመንግሥት ለውሳኔ ማቅረብ፣

፭/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ሀይል ግዥ ስምምነቶችንና ሌሎች የፕሮጀክት ስምምነቶችን ጨምሮ የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣

፮/ ለእያንዳንዱ ጨረታ ማስታወቂያ ዝቅተኛ የጨረታ ዋጋ እና ተቀባይነት ያለው የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ወይም ሌላ የክፍያ አማራጭን ማዘጋጀት፣

፯/ ለጨረታ ማስከበሪያና ይፋ ላልሆነ ስምምነት ማስፈፀሚያ ክፍያ ለከፈሉ በጨረታ መወዳደር ለሚችሉ ተጫራቾች በቀላሉ ሊያገኙት የሚችሉትን መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስ ማዘጋጀት፣

፰/ ስለጨረታው በተገቢው መንገድ ይፋ ማድረግ፣

## PART FIVE
## BIDDING

### 27. Competitive Bidding

The Licensing Authority may issue Exploration Licenses and Grade I Well-field Development and Use Licenses by competitive bidding as provided in Article 17 of the Proclamation and this Regulation.

### 28. Responsibilities and Authorities of the Licensing Authority

The Licensing Authority shall follow the following requirements in tendering a license area for bid tender:

1/ Establish a schedule for the bid tender and selection process;

2/ Determine the area available for bid;

3/ Establish technical and financial minimum qualifications for incorporation in bid packages;

4/ In process for evaluation of bids, including evaluation criteria relating to the establishment of the power plant, the generation of electricity, and the tariffs charged by generation licensees; review national grid related tariffs submitted to it by licensee and submit its recommendation to the government in accordance to Article 4(3) of Energy Proclamation No. 810/2013;

5/ Prepare bid documents, including, for Grade I Well-field Development and Use Licenses, terms of a power purchase agreement, and other project agreements as applicable;

6/ Establish the minimum bid amount and the terms of acceptable cash payment or other financial arrangements, for each bid tender;

7/ Establish a secure electronic data room to be accessible by potential bidders only upon payment of fee for the bid package and execution of a non-disclosure agreement;

8/ Announce the tender through appropriate means;

፱/ የቀረቡ ጨረታዎችን መገምገም፣

፲/ አሸናፊውን ተወዳዳሪ መለየት፣

፲፩/ ለአሸናፊ ተጫራች ስለሚሰጠው የፈቃድ ጊዜ ድርድር ማድረግና ማጠናቀቅ ወይም ምንም አሸናፊ ተጫራች ከሌለ የታቀደውን የፈቃድ ክልል በውድድር ከሚሰጥ ጨረታ ማውጣት ወይም ለምርመራ ፈቃድ ከጨረታው ማስታወቂያ በፊት አንድ አመልካች ካመለከተ የጨረታው ሂደት እንዳለቀ አመልካቹን መግለፅ እና አመልካቹ የዚህን ደንብ አንቀፅ ፬ ቅድመ ሁኔታ ካሟላ ፈቃዱን መስጠት፣

፲፪/ ክፍያዎች መሰብሰብና የጨረታ ማስያዣውን እንዳስፈላጊነቱ ማረጋገጥ፣ እና

፲፫/ ውጤቱን ለተጫራቾች ማሳወቅ እና ከውጤቱ በኋላ ባሉት ሰላሳ (፴) ቀናት ውስጥ ተጫራቾች ለሚያቀርቡት ጥያቄ ስለ ጨረታው ግምገማ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት::

## ፳፱. የጨረታ ሰነድ

የጨረታ ሰነድ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ወይም ጨረታውን ለመመዘን ብቃት ያላቸው ቴክኒካል ባለሙያዎችን በማካተት በሚቋቋም የጨረታ ኮሚቴ ይዘጋጃል፣ የጨረታ ሰነዱን ተወዳዳሪዎች በሚጠይቁበት ጊዜ እና አስፈላጊውን ክፍያ ከፈጸሙ በኋላ ይቀርብላቸዋል፣ የጨረታ ሰነዱ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ክፍል የሚገኝ ሲሆን የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይችላል:-

፩/ የጨረታ ማመልከቻ ማስገቢያ እና መክፈቻ የጊዜ ገደብ፣

፪/ አሸናፊውን ተጫራች መለያ የመመዘኛ እና የመምረጫ መስፈርቶች እና ሂደት፣

፫/ ለደረጃ Ⅰ ጉድጓድ ማልማት እና መጠቀም ፈቃድ የሚቀርብ ጨረታ የደረጃ Ⅰ ጉድጓድ ማልማት ፣ መጠቀም እና የሃይል ማመንጨት ረቂቅ ሞዴል የያዘ ሰነድ፣

፬/ አነስተኛ የጨረታ ዋጋው፣

፭/ በጨረታው አሸናፊ የሆነው የአከፋፈሉ ሁኔታ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

9/ Evaluate bids received;

10/ Identify a prospective successful winning bid;

11/ Negotiate and finalize terms of a license to be issued to the successful bidder, or if no winning bid is received, withdraw the proposed License Area from competitive consideration; or, for Exploration License, if an application has been submitted by one applicant prior to the bid tender, declare the bid process complete and the applicant, if its application meets the licensing requirements of Article 4 of this Regulation, issue a license;

12/ Collect fees and ensure posting of adequate bonds as required; and

13/ Inform bidders of the outcome of the bidding process and, upon request by a bidder within 30 days of the receipt of the outcome, provide a debriefing to that bidder on the evaluation of its bid.

## 29. Bid Package

A bid package shall be assembled by the Licensing Authority or a bid evaluation committee including technically competent members. The bid package shall be made available to prospective bidders upon request and payment of the applicable fee. The bid package shall be available at a electronic data room established for the purpose, upon payment of a fee, and shall contain the following information:

1/ Deadline for submission and opening of bid proposals;

2/ Evaluation criteria and selection process for determining the winning bid;

3/ For Grade I Well-field Development and Use, a model Grade I Well-field Development and Use License and Model Power Generation License containing the proposed terms and conditions of a license including exhibits and other documentation;

4/ Minimum bid amounts;

5/ Terms of payment of bid amounts by the winning bidder, including

ሀ) የጨረታው አሸናፊ በሚገለጽበት ጊዜ የሚከፈል ከአጠቃላይ የጨረታ ዋጋው ቢያንስ ሃያ በመቶ (፳%)፣ እና

ለ) ቀሪው የጨረታ ዋጋ ክፍያ የባለፈቃዱ የረጅም ጊዜ የፕሮጀክት ሂሳብ መዝጊያ ጊዜ ወይም በሀይል ማመንጫ ጣቢያው ሥራ ማስጀመሪያ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ከሁለቱ በቀደመው ሊሆን ይችላል፡፡

፮/ አሸናፊው ተጫራች ከቀረበው የገንዘብ ማስያዥያ በመነሳት፣ የሚጠበቅበት ክፍያ ወይንም የዋስትና ቦንድ ወይንም ሌላ ማስያዥያ::

፯/ ለደረጃ 1 የጉድጓድ ማልማት እና መጠቀም ፈቃድ ረቂቅ የሀይል ግዥ ሰነድ እና ሌሎች የፕሮጀክት ሰነዶች፣ እና

፰/ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተረጋገጡ እና የዚህን ደንብ ተፈፃሚነት የሚያረጋግጡ ሌሎች አጠቃላይ መረጃዎች ወይም ማስረጃዎች::

## ፴. ስለ ጨረታ ውድድር ለህዝብ የማስተዋወቅ ሂደት

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጨረታውን ለማስጀመር የሚያደርገውን የማስታዎቂያ ጥሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ እና/ወይም በፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ድረ- ገፅና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች የመወዳደሪያ የጨረታ ማስታዎቂያውን ያቀርባል፡፡

፪/ ጨረታውን ለማስጀመር የሚደረገው ጥሪ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) የጨረታ ውድድር ይሸፍነዋል ተብሎ የሚታሰበው የፍቃድ ቦታ ስም ወይም የስያሜ ቁጥር፣

ለ) ሥፍራውን የሚያሳይ ካርታ፣ የታቀደውን ፍቃድ ወሰን የሚገልጽ የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮኦርዲኔት እና ማግኘት ከተቻለ የሳተላይት ምስል፣

ሐ) ተጫራቹ ከኤሌክትሮኒክስ የጨረታ መረጃ ክፍል መረጃ ማግኘት የሚችልበት መንገድ፣ ለጨረታ ሰነዱ የሚያስፈልግ ክፍያ፣ ይፋዊ ያልሆነ ስምምነትን የሚገልጽ መረጃ፣ እንዲሁም ለተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፣

a) payment of a minimum of 20% of the total bid amount at the time of bid award; and

b) payment of the remainder of the bid amount at the time of Licensee's closing of long term project financing or within one year of power plant commissioning, which ever is earlier.

6/ Requirements of payments and or posting of performance bonds or other security by a successful bidder, which requirements may be based on the type of financial terms offered.

7/ For a Grade 1 Well-field Development and Use License, preliminary terms of a power purchase agreement and other project documents, and

8/ All other information or materials determined by the Licensing Authority relevant to effective implementation of this regulation.

## 30. Publication of Notice of Bids for Competitive License Bid Tender

1/ The Licensing Authority shall provide notice of a License Bid Tender publicize through public mass media having wider access and or through the Licensing Authority website.

2/ The call to start the bidding shall contain the followings:

a) name or designator number of the proposed license area covered by the bid tender;

b) maps showing the location of the proposed license area with global positioning system coordinates and if available satellite images;

c) information regarding where the bidder may secure a bid package and access to the bidding electronic data room, required payment for bid package, and sign post of a non-disclosure agreement, and also bid security bond;

መ) የጨረታው መቀበያ እና የጨረታው መክፈቻ ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት ፤ የጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ ማስያዣ መጠንና ክፍያ፤ እና

ሠ) በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በሚወሰን ተሳታፊነትን የሚያበረታታ ሌላ መረጃ፡፡

## ፴፩. ስለጨረታ አቀራረብ

ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተመለከቱት መስፈርቶች መሠረት አስፈላጊ ሰነድ ማቅረብ እንዲሁም፡

፩/ የጨረታውን ሰነድ በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ማቅረብ፤

፪/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባዘጋጀው ፎርም እና አሰራር መሠረት የጨረታውን ሰነድ ማቅረብ፤

፫/ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተረጋገጠ የጨረታ ማስከበሪያ በእያንዳንዱ ጨረታ ማካቲት፤

፬/ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተጠየቀው መሠረት የቴክኒክ አቅም፣ የሥራ ፕሮግራም፣ ተያያዥነት ያለው የበጀት መጠን፣ በሥራ ፕሮግራሙ መሠረት የጊዜ ሰሌዳ እና ጨረታው ካለፈ ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከአበዳሪ ድርጅቶች ጋር የተፈፀሙ ስምምነቶችን የሚያሳይ ደብዳቤ አያይዞ ማቅረብ፤

፭/ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የቀረበ የፋይናንስ እቅድ ማቅረብ፤

፮/ የተሟላ የፍቃድ ማመልከቻ ማቅረብ፤

፯/ በመጫረቻ ፖስታው ላይ የፍቃድ ቦታው ስምና የስያሜ ቁጥር እና "በጨረታው ማስታዎቂያ ላይ ከተገለፀው ቀን በፊት እንዳይከፈት" በመጻፍ ከጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ ጋር በማያያዝ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው አድራሻ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ሁለት (፪) ኤሌክትሮኒክ ኮፒ በማያያዝ ማስገባት፤

፰/ በተጫራቾች መካከል ግጭት ወይንም ማስፈራራት የተከለከለ መሆኑን ማስገንዘብ፡፡

d) the place, dates and time for acceptance of bids and bid opening, amount of the bid bond required, and fees; and

e) other information as determined by the Licensing Authority to encourage participation in the proceedings.

## 31. Submittal of Bids

Bidders must submit bids in a form and with contents that are consistent with the requirements of the bid package and notice, and shall:

1/ Submit bids during on the specified time period;

2/ Submit bids in a form and by a method specified by the Licensing Authority;

3/ Include in each bid the bid bond as determined by the Licensing Authority;

4/ Submit technical information as required in the bid package, a work program and associated budget, schedule for execution of the work program, and letter of commitment by financial backers committing to the project should the bid be successful;

5/ Provide a financial proposal of a type prescribed in the bid package;

6/ Provide a complete license application; and

7/ Label each envelope containing a bid with the license area name or number and the statement "Not to be opened before [date posted in the tender notice]'' and submit the envelope with required bond to the Licensing Authority office by the date and time specified in the bid package, together with two electronic copies addressed to the address specified.

8/ Understand that collusion amongst bidders or intimidation of bidders is prohibited.

**፴፪. በጨረታ ውድድር ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ መመዘኛዎች**

፩/ በጨረታ አማካኝነት ለሚገኙ ፈቃዶች ተጫራቹ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

፪/ ተጫራቾች እንደ አስፈላጊነቱ ቦንድ ያስይዛሉ፡፡

፫/ ተጨራቾች ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያቀርበውን የቴክኒክና የፋይናንስ መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፡፡

፬/ አንድ ተጫራች የጨረታው መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ ጨረታውን ማቋረጥ አይችልም፤ ጨረታውን መላክ በጨረታው ለመወዳደር ሕጋዊ ግዴታ ሆኖ ያገለግላል፡፡

**፴፫. ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ**

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ጨረታን ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው፡-

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ካስቀመጠው ዝቅተኛ የጨረታ ዋጋ በላይ የሆነ ጨረታ ከሌለ፤ እና

፪/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ያስቀመጠውን የቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም መስፈርትን የሚያሟላ ተጫራች እንደሌለ ካረጋገጠ፡፡

**፴፬. ስለጨረታ ሂደት እና አሸናፊነት**

፩/ ጨረታዎች ማስታዎቂያ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ዘጠና ቀናት ውስጥ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

፪/ የጨረታው ማስታዎቂያ በጋዜጣ ከወጣ ከዘጠና ቀናት በኋላ በማስታዎቂያው ላይ በተገለፀው ጊዜ ለህዝብ ክፍት ሆኖ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ይከፈታል፡-

ሀ) ጨረታው የሚከፈተው የቀረቡትን ጨረታዎች ለህዝብ ለማሳወቅ እና ለመመዝገብ ነው፤

ለ) በዚህ ጊዜ ማንኛውንም ዓይነት ጨረታ መቀበልም ሆነ ውድቅ ማድረግ አይቻልም፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተጫራቾችን ሰነድ ለጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤የጨረታ ኮሚቴው ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ የቴክኒካል እና ፋይናንስ ሁኔታ በመገምገም አሸናፊውን ይገልጻል፡፡

**32. Minimum Requirements for Participating in the Bid**

1/ For licenses that may be issued as a result of the bid tender, the bidder must meet the requirements of the Proclamation and this regulation.

2/ Bidders shall post bonds as required.

3/ The bidder must meet technical and financial qualifications and terms established by the Licensing Authority.

4/ A bidder may not withdraw a bid after closing of the bid acceptance period. Submittal of a bid constitutes a legally binding commitment by the bidder.

**33. Rejection of Bid**

The Licensing Authority may reject a bid if:

1/ there is no bid above a minimum bid amount set by the Licensing Authority; and

2/ the Licensing Authority determines that no bidder meets the technical or financial qualifications in the bid package.

**34. Bidding Process and Award**

1/ Bids shall be submitted within 90 days from the issuance of the bid notice.

2/ Secure bids received in response to the notice of license bid tender shall be opened by the Licensing Authority at a public bid opening on the 90th day following notice of bid tender, at an hour specified in the notice.

a) the opening of bids is for the sole purpose of publicly announcing and recording the bids received;

b) no bids shall be accepted or rejected at that time.

3/ The Licensing Authority shall provide the bids to the Bid Evaluation Committee. The Bid Evaluation Committee, on condition of confidentiality, evaluates its assessment of the qualifications on technical and financial terms of the award and its recommendation of the most qualified bidder.

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ ጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴው ያቀረበውን የግምገማ ውጤት ከግምት ውስጥ በማስገባት ያጸድቃል፡፡ ነገር ግን በጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴው ውጤት የማይስማማ ከሆነ ጉዳዩን ከቀረበው ምክንያት ጋር ይመልሰዋል፡፡

፭/ ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ባሉት ሃያ (፳) ቀናት ውስጥ ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ ላስያዙ ተጫራቾች ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፮/ ጨረታው ላሸናፊው ከተገለጸና ከተላለፈ በስልሳ ቀናት ውስጥ በፍቃድ ሰጪው የተዘጋጁ ሁለት ኦሪጅናል የፍቃድ ሰነዶች እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት ያለው የሀይል ግዥ ስምምነት እና ሌሎች የፕሮጀክት ሰነዶች ከአሸናፊነት ማስታዎቂያ ጋር ለጨረታው አሸናፊ ይላካል፡፡

፯/ ተጫራቹ ፈቃዱ ከተላለፈለት በኋላ ከአስራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፍቃዱን አሸናፊ ስለመሆኑ እውቅና እና ተያያዥ ዶክመንቶችን ጨምሮ የፍቃድ ውሎችን መቀበሉን ለማረጋገጥ በሁለቱም ዋና የፍቃድ ሰነዶች ላይ ይፈርማል፡፡ የተፈረመበትን እያንዳንዱን የፍቃድ ዶክመንት ለፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ይመልሳል፡፡ በመመሪያው እንደተቀመጠው ለክልሎች የአንድ ዓመት የመሬት ኪራይ ክፍያ እና ሌሎች በጨረታው ላይ የተቀመጡትን ክፍያዎች ይከፍላል፡፡

፰/ የጨረታው አሸናፊ ፈቃዱን እንደወሰደ ለተቀሩት ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብ ይመለስላቸዋል፡፡

፱/ አንድ አሸናፊ ተጫራች በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የፈቃድ ውሉን ካልፈፀመ ለጨረታ ያስያዘው ገንዘብ ተወርሶ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈንድ ውስጥ ይቀመጣል፡፡

፲/ የፍቃድ አሸናፊው የተፈፀመው በህጋዊ ወኪል በኩል ከሆነ፣ ህጋዊ ወኪሉ ጉዳዩን ማስፈፀም እንደሚችል የሚገልጽ የቦታውን ስም ወይንም መለያ ቁጥር የያዘ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

4/ The Licensing Authority shall approve by considering the recommendation of the Bid Evaluation Committee in selecting the winning bid. If the Licensing Authority does not agree with the recommendation of the Bid Evaluation Committee, it shall refer the matter back with the reasons for its decision.

5/ Within 20 days of the bid opening, the Licensing Authority shall provide written notice of the final decision on the bids to those bidders whose bonds have been posted in accordance with instructions set forth in the notice of bid tender.

6/ If a bid is awarded, within 60 days, two (2) originals of the license, executed by the Licensing Authority, including fully executed power purchase agreement and other project documents, shall be transmitted with the notice of acceptance to the successful bidder;

7/ the bidder shall, not later than the 15th day after receipt of the license, shall sign both originals of the license as acknowledgement of receipt and acceptance of license terms including terms of associated documents, and shall return every signed original documents of the license to the Licensing Authority, together with the first year's regional State rental as provided in directives, any other fees as identified in the bid documents, and minimum payments;

8/ security bonds shall be released for rejected bids, upon acceptance of the license by a successful bidder.

9/ If a successful bidder fails to execute the license within the prescribed time, its bond shall be forfeited and deposited in the Licensing Authority fund.

10/ If the awarded license is executed by an attorney-in-fact acting on behalf of the bidder, evidence should be submit that verify the bidder authorized the attorney-in-fact to execute the license on its behalf, and Reference to the name or number of the License area.

፲፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፱ የጂኦተርማል ሃብት ምዝገባ እንዲሁም በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ስለ መረጃው መመዝገቡ በጽሁፍ ለባለፍቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

11/ The fully executed license shall be recorded in the Register of Geothermal Resources, as provided in Article 9 of the Proclamation and this regulation, and the Licensing Authority shall provide written confirmation of recording to the Licensee.

፲፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለውድድር የታቀዱ ቦታዎች ላይ ለመወዳደር የቀረቡ ጨረታዎችን በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ሊሰርዝ ይችላል፤ ነገር ግን ከጨረታ መወዳደሪያው ዝቅተኛ ዋጋ በላይ የሚቀርቡ ጨረታዎችን ላይሰርዝ ይችላል፡፡

12/ The Licensing Authority may reject any and all bids received for any area proposed for bid tender; provided, however, that the Licensing Authority may not reject bids that exceed a minimum threshold on the basis of bid amount alone.

## ፴፭. <u>የጨረታ አሸናፊው የአከፋፈል ሁኔታ</u>

## 35. <u>Submittal of Payments Following Bid Award</u>

፩/ የተመረጠው ተጫራች በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ባለው መልኩ ክፍያዎችን መፈጸም አለበት፡፡

1/ The selected bidder must make payments by means deemed acceptable by the Licensing Authority.

፪/ የጨረታው አሸናፊ በሚገለጽበት ቀን የሥራ ሰዓት ሳይጠናቀቅ ወይም የፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን በሚወስነው ሌላ ጊዜ አሸናፊው ተጫራች ለእያንዳንዱ የፍቃድ ቦታ የሚከተሉትን ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ) በጨረታ ሰነዱ ውስጥ እንደተመለከተው በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያለው የክፍያ ሁኔታ እና ወይም የውል ስምምነት፤

ለ) ለመጀመሪያው ዓመት የመሬት ኪራይ ክፍያ፤ እና

ሐ) መፈፀም ያለባቸው የፈቃድ ክፍያዎች፡፡

2/ By the close of official business hours on the day of the bid award or such other time thereafter as the Licensing Authority may specify, the successful bidder must submit for each license area:

a) financial payment or arrangement and/or pledge of security acceptable to the Licensing Authority, as provided in the bid package;

b) the full amount of the first year's land rent fees; and

c) applicable license fees.

፫/ የጨረታው አሸናፊ በሚኖረው የፋይናንስ ውል እና የጊዜ ገደብ መሠረት ተጨማሪ ክፍያዎችን ሊፈፅም ይችላል፡፡

3/ Additional payments by the selected bidder shall be made within a timeframe consistent with financial terms established pursuant to bid award.

፬/ የጨረታው አሸናፊ የሚጠበቅበትን ክፍያ መፈፀም ካልቻለ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የጨረታውን ተቀባይነት ማገድ እና የተላከውን ማንኛውም ገንዘብ መያዝ ይችላል፤ እንዲሁም ተጫራቹ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በቅጣት መልክ ይከፍላል፡፡

4/ If a successful bidder fails to make all payments required under this section the Licensing Authority may revoke acceptance of the bid and keep all money that has been submitted; and the bidder shall forfeit its bid bond to the Licensing Authority.

## ፴፮. <u>ስለተቃውሞ አቀራረብ</u>

## 36. <u>Submittal of Objections</u>

፩/ ተጫራቾች የጨረታው ውጤት ከተገለጸ በኋላ ባሉት አስር የሥራ ቀናት ውስጥ የቅሬታቸውን አሳማኝ ምክንያት እና መረጃ በጽሁፍ በመግለጽ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

1/ Bidders may submit objections to the Licensing Authority in writing based on an assertion of deviation from the procedure stipulated in bid documents. An objection shall include specific reasons for objection

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተቃውሞውን ከተቀበለ በኋላ ተቃውሞው ውሳኔ እስኪያገኝ የጨረታና የፈቃድ ሂደቱን እና ከጨረታው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክንውኖች በማቆም በሚቀጥሉት አስር የሥራ ቀናት ውስጥ መርምሮ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ በጨረታው ተሳታፊ የቀረበ ተቃውሞ የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ከሆነ ጨረታው በድጋሚ ሊታይ ወይም ደግሞ በፍቃድ ሰጪው ውሳኔ መሠረት ጨረታው ሊደገም ይችላል፡፡

**፴፯. ስለይሁንታ ፈቃዶች እና ማረጋገጫዎች**

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ከታክስ አተገባበር እና ከጉምሩክና ቀረጥ ነፃ ከመሳሰሉ ለባለፈቃዱ ከሚያስፈልጉት የተለያዩ የይሁንታ ፈቃዶችና ማረጋገጫዎች ኃላፊነቱን በአግባቡ በመወጣት እና በመተግበር በሚመለከተው የኢትዮጵያ ሕጎችና ደንቦች መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ስለደረጃ I የጂኦተርማል ቁፋሮ ሥራዎች

**፴፰. ለቁፋሮ ሥራዎች አግባብነት ያላቸው አጠቃላይ መስፈርቶች**

፩/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ልማት ቁፋሮ ሥራዎች የቁፋሮ ፈቃድና ለሥራዎቹ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በተመለከተ በዚህ ደንብ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር ሁሉም ከጉድጓድ ቁፋሮ በፊት የሚከናወኑ አስፈላጊ የመሠረተልማት ዝርጋታ እቅድና ልማት እና ለተመሳሳይ ሥራዎች የሚከናወኑ የፍሎው ቴስት፣ ጂኦተርማል ፈሳሾችን የማውጣት፣ ፈሳሾችን መልሶ ወደ ጂኦተርማል ሪዘርቫየሩ ሪኢንጀክት ማድረግ ወይንም ጉድጓዶችን መዝጋትና መተው በዚህ ክፍል መሠረት መተግበር አለባቸው፡፡

and facts supporting the objection, and shall be submitted to the Licensing Authority within ten (10) working days from notification of the bid outcome.

2/ Upon receipt of an objection, the Licensing Authority shall immediately cease processing bid documents or licenses or any other ancillary processes or documents relating to that bid, pending resolution of the objection, and shall provide its response within ten (10) working days from the receipt of the objection letter.

3/ In the event the objection is supported by the facts provided by the bid participant, the bids may be re-evaluated based on the outcome of the objection, or the bidding process may be repeated, in the discretion of the Licensing Authority.

**37. Permits and Other Approvals**

The Licensing Authority shall provide reasonable assistance to a Licensee in securing the necessary permits and other approvals required under the laws and regulations of Ethiopia, including but not limited to approvals related to tax treatment, customs and import duties; provided, however, that the Licensee shall at all times be fully responsible to secure and comply with all permits and permissions required under the laws of Ethiopia.

## PART SIX
## GRADE I GEOTHERMAL DRILLING OPERATIONS

**38. General Standards Applicable to Drilling Operations.**

1/ Regarding the requirements for Grade I geothermal resource development drilling operations, unless otherwise provided in this regulation, all planning and development of infrastructure required prior to drilling a well and conduct of related activities for the purpose of performing flow tests, producing geothermal fluids, re-injecting fluids into a geothermal reservoir, or plugging and abandonment of wells shall be conducted consistent with the provisions of this part of the Regulation.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ የቁፋሮ ሥራዎች የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ) ሁሉንም የአካባቢ ደህንነት መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት፤

ለ) የጂኦተርማል ሀብቱን መጠበቅ እና ብክነትን መቀነስ፤

ሐ) በመሬት ላይ እና በከርሰ ምድር በሚገኙ በሌሎች ሀብቶች ላይ አላስፈላጊ ተፅዕኖዎችን እንዳያደርሱ መከላከል፤

መ) የህዝብን እና የሠራተኛን ጤንነትና ደህንነት አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በመከተል መጠበቅ፤

ሠ) በዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ በመመርኮዝ የሚወጡ መመሪያዎችን መከተል፤

ረ) በአዋጁ እና በዚህ ደንብ የተቀመጡ ሁሉንም መስፈርቶችን ማሟላት፡፡

## ፴፱. በፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የሚፀድቁ እና የሚሰጡ የይሁንታ ፈቃዶች

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አግባብ ባለው ሁኔታ የሚከተሉትን ሊያፀድቅ ወይም የይሁንታ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) የቁፋሮ ዕቅድና ፕሮግራም፤

ለ) ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ፤

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ፕሮግራሙን ሳያጸድቅለት ባለፈቃዱ በቁፋሮ ፕሮግራሙ የታቀዱ ምንም አይነት ሥራዎችን መጀመር አይችልም፡፡

፫/ በባለፈቃዱ በፀደቀ የቁፋሮ ዕቅድ፣ የቁፋሮ ፕሮግራም እና የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጽሁፍ የተደረገውን ለውጥና ለለውጡ ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በማብራራት የግምገማ ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡

## ፵. የቁፋሮ ዕቅድ ስለማፅደቅ

፩/ ባለፈቃዱ የቁፋሮ ዕቅዱን ለማፅደቅ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፡-

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, drilling operations must:

a) Meet all environmental standards;

b) Conserve geothermal resources and minimize waste;

c) Prevent unnecessary impacts to other surface and subsurface resources;

d) Protect public and worker health and safety in compliance with applicable laws;

e) Be conducted according to directives to be issued in accordance with international best practices; and

f) Comply with all requirements as may be established by the Proclamation and this Regulation.

## 39. Approval and Issuance of Permits by the Licensing Authority.

1/ The Licensing Authority shall approve, or issue permit as appropriate, to:

a) drilling plans and programs;

b) well design plan and drilling permit applications for a single or multiple wells.

2/ The Licensee may not start any activities described in the drilling program until the Licensing Authority approves the drilling program

3/ Any change by the Licensee to the approved drilling plan, drilling program and well design plan shall be submitted to the Licensing Authority together with an evaluation report with justifications for the changes.

## 40. Approval of Drilling Plan

1/ The Licensee to approve the drilling plan must provide to the Licensing Authority:

ሀ) የቁፋሮ ፕሮጀክቱን የተሟላ የልማት እቅድ፣

ለ) የጤንነትና ደህንነት ዕቅድ፣ እና

ሐ) የመጀመሪያ ደረጃ የማመሳከሪያ የአካባቢ እና ማህበረሰብ ዳሰሳ ጥናት፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ዕቅዱ ሁሉንም የሕግ እና የቴክኒካል መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ማመልከቻ በተቀበለ አስራ አምስት (፲፭) የሥራ ቀናት ውስጥ ሊያፀድቀው ይችላል፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ዕቅዱን ካላፀደቀ ባለፈቃዱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት የተሻሻለ ፕሮግራም እንዲያቀርብ ለማስቻል ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያላፀደቀበትን ምክንያት በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፬/ ባለፈቃዱ የቁፋሮ ዕቅዱ ከፀደቀለት በኋላ የሥራ ቦታ ማሻሻያን የመጀመር እና በተጨማሪም የአካባቢ ጥናት እና ማህበረሰብ አጠባበቅ ሥራ ሊያከናወን ቢችልም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለአንድ ወይንም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች የቁፋሮ ፕሮግራም እና የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እስኪያጸድቅና የቁፋሮ ፈቃድ እስኪያገኝ ድረስ የቁፋሮ ሥራ መጀመር አይችልም፡፡

## ፵፩. የቁፋሮ ፕሮግራም ስለማፅደቅ

፩/ የቁፋሮ ፕሮግራም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለዚሁ ተግባር በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ፕሮግራሙ ሁሉንም የሕግ እና የቴክኒካል መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ማመልከቻ በተቀበለ አስራ አምስት (፲፭) የሥራ ቀናት ውስጥ ሊያፀድቀው ይችላል፡፡

፫/ የቁፋሮ ፕሮግራሙ ለእያንዳንዱ ጉድጓድ የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን ለመገምገም በቂ መረጃ መስጠት የሚኖርበት ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የጉድጓድ መቆፈሪያ መደብ አቀማመጥ እና ንድፍ፣

ለ) የነባርና አዲስ ለታቀዱ የመዳረሻ መንገዶች ሁኔታ ማብራሪያ፣

ሐ) ማናቸውም አስፈላጊ የድጋፍ አገልግሎት መስጫና የመሠረተ ልማት አውታሮች ማብራሪያ፣

a) a complete plan of development of the drilling project;

b) a health and safety plan; and

c) baseline environmental community assessment study.

2/ After receiving the application for the drilling plan the Licensing Authority, within fifteen (15) working days, may approve the drilling plan if it complies with all legal and technical requirements.

3/ If the Licensing Authority refuses to approve the drilling plan, it shall notify to the Licnsee in writing the reasons thereof in order for the Licensee to submit a revised program as per the reasons given by the Licensing Authority.

4/ The Licensee may initiate site improvements upon approval of the drilling plan , including environmental assessment and social and community safeguards; provided, however, that the Licensee may not start any drilling operations until the Licensing Authority has approved the drilling program and well design plan and drilling permit for one or more wells.

## 41. Approval of Drilling Program

1/ A drilling program shall be submitted in the form prescribed for such purposes by the Licensing Authority.

2/ After receiving the application for the drilling program the Licensing Authority, within fifteen (15) working days, may approve the drilling program if it complies with all legal and technical requirements.

3/ The drilling program must provide sufficient information to assess the environmental and social impacts of the proposed operations for each well, including:

a) well pad layout and design;

b) a description of existing and planned access roads;

c) a description of any ancillary facilities/infrastructure required;

መ) ለጉድጓድ መቆፈሪያ መደብ እና ለመንገድ መገንቢያ የሚሆኑ ግብዓቶች መገኛ፣

ሠ) የውሃ መገኛዎች፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ዓላማ፣ መጠን እና የመጠቀም ፈቃድ፣

ረ) የቁፋሮ ቦታውን ገፀ-ምድር ወደነበረበት ይዞታ የመመለስ ዕቅድ፣

ሰ) አካባቢን እና ሌሎች ሀብቶችን ለመጠበቅ የሚከናወኑ ተግባራት ማብራሪያ፣

ሸ) የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት፣

ቀ) የማህበራዊና ማህበረሰብ ጥናት ግምገማና አደጋ መከላከያ እርምጃዎች፣እና

በ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ምክንያታዊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን በሚወጣ መመሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ፕሮግራሙን ካላፀደቀ ባለፈቃዱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት የተሻሻለ ፕሮግራም እንዲያቀርብ ለማስቻል ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያላፀደቀበትን ምክንያት በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## ፵፪. የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና ጉድጓድ ቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ማመልከቻ

፩/ ባለፈቃዱ የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ማመልከቻ ከቁፋሮ ፕሮግራም ጋር በአንድ ላይ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ ለእያንዳንዱ ጉድጓድ መቅረብ ያለበት ሲሆን ንድፉ አመቺ መሆኑን ምክንያታዊ በሆነ በግልጽ ለመወሰንና ለመረዳት የሚያስችል በቂ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡በተጨማሪም የጂኦሎጂካል ኢላማ ቦታዎችን፣ ማናቸውም የታቀደ አግድማዊ ቁፋሮ እና ዝርዝር የጉድጓድ ኬዚንግ ፕሮግራምና የሚጠቀሙበት ቁሳቁስ መረጃዎች ማብራሪያ ማካተት ይኖርበታል፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ሁሉንም የሕግ እና የቴክኒካል መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ማመልከቻውን በተቀበለ አስር የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት የሚኖርበት ሲሆን በነዚህ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ የጉድጓድ ንድፍ ዕቅዱ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ጥያቄው እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

d) the source of drill pad and road building material;

e) the water source, purposes of use, quantities and use permit;

f) plans for surface recuperation of the drilling area;

g) a description of procedures to protect the environment and other resources;

h) environmental impact assessment study;

i) social and community study assessment and safeguard measures; and

j) any other information as may reasonably be requested by the Licensing Authority to be determined by the directives.

4/ If the Licensing Authority refuses to approve the drilling program, it shall notify to the Licensee in writing the reasons thereof in order for the Licensee to submit a revised program as per the reasons given by the Licensing Authority.

## 42. Well Design Plan and Drilling Permit Application

1/ The Licensee can submit well design plan and drilling permit application together with its drilling program.

2/ The well design plan must be for each individual well and shall provide sufficient information to allow for an objective determination as to the suitability of the design, including description of the geological target areas, any proposed directional drilling, and the detailed well casing program and materials.

3/ The Licensing Authority shall give its decisions within 10 (ten) working days of receipt of the application, if the drilling plan and drilling permit complies with all legal and technical requirements, if no decision is issued within 10 (ten) days, the well design plan shall be deemed to be approved.

**፵፫. ከአንድ ጉድጓድ በላይ ለመቆፈር ስለሚቀርብ ጥያቄ**

፩/ የባለፈቃዱ የቁፋሮ ፕሮግራም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች ሊተገበር የሚችል ቢሆንም የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራው በተመሳሳይ ሁኔታ የሚካሄድ ከሆነና እና ቀድሞ ከተደረገ ሳይንሳዊ የስነምድር ጥናት ውጤት በመነሳት ተመሳሳይ የጂኦሎጂና የጂኦተርማል ፈሳሽ ክምችት ሁኔታ እንደሚጠብቀው ካመነ መሆን አለበት፡፡

፪/ ባለፈቃዱ የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ለእያንዳንዱ ለሚቆፈረው ጉድጓድ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን እንዲሁም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች በተመሳሳይ ጊዜ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፵፬. የቁፋሮ ሥራዎችን ስለማካሄድ**

የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ለማካሄድ ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊትና በቁፋሮ ጊዜ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል፡-

፩/ የጂኦተርማል ጉድጓድ ቁፋሮውን በቁፋሮ ፕሮግራሙ መሠረት እና ለባለፈቃዱ ከፀደቀው የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ጋር በሚጣጣም መልኩ ለመቆጣጠር የሚችል በጂኦተርማል ጉድጓድ ቁፋሮ ብቁ የሆነ ባለሙያ ያለው፣

፪/ ተገቢውን የደህንነት ጥበቃ አሰራር በመቅረጽና በመተግበር ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የደህንነት ጥበቃውን በሚመለከተው የሕግ ማዕቀፍ መሠረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ ወይንም የሕግ ማዕቀፉ በሌለበት ሁኔታ በአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የአሰራር ኮድ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ባገናዘበ መልኩ የሚያረጋግጥ ባለሙያ ያለው፣

፫/ ለባለሙያዎቹ በመደበኛ እና በአደጋ ጊዜ አሰራሮችን ፈጣን እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወን የሚያስችላቸው ስልጠና መስጠት፣

፬/ በአግባቡ ለሥራ ብቁ የሆኑ መሳሪያዎችን የሚጠቀም፣

፭/ ፈጣን እና ውጤታማ የሆነ የአስቸኳይ አደጋ ምላሽ የሚሰጡ የአፈፃፀም አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣

**43. Application for Drilling More than One Well**

1/ The Licensee's drilling program may apply to more than one well, provided the Licensee will drill the wells in the same manner and expects to encounter similar geologic and reservoir conditions based on the result of scientific geological studies undertaken.

2/ The Licensee must submit well design plan and drilling permit applications for each well to be drilled, and may submit applications for multiple wells simultaneously,.

**44. Conducting Drilling Operations**

Prior to drilling a well and during the drilling, the Licensee must follow the following operational requirements for drilling:

1/ Have geothermal well drilling qualified professional responsible for overseeing implementation of the Licensee's drilling program and ensuring compliance with the Licensee's approved well design plan and drilling permits;

2/ Have a qualified professional responsible for establishing and maintaining safety procedures and certifying to the Licensing Authority that such procedures comply with the relevant laws of the country or in the absence of such laws, directives to be issued in accordance with the African Union Code of Practice for Geothermal Drilling;

3/ Conduct training, to ensure its personnel are capable of performing standard and emergency procedures quickly and effectively;

4/ Use properly maintained equipment;

5/ Implement operational practices that allow for quick and effective emergency response;

፮/ በጉድጓድ ቁፋሮ ወቅት ሁሉንም ሥራዎች መቆጣጠር፣ የእያንዳንዱን ጉድጓድ ቁፋሮ ከመነሻ እስከ ማጠናቀቂያው በመከታተል በየቀኑ የሚከናወኑ ሥራዎችን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል አሰራር መዘርጋትና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እነዚህን ሪፖርቶች እንደአስፈላጊነቱ በሚጠየቅበት ጊዜ ማቅረብ፣

፯/ ጉድጓዶቹ ሁልጊዜ በቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ እና

፰/ የደህንነት ጥበቃን በተመለከተ ውይይቶችን በመደበኛነት ማድረግ፡፡

፵፭. <u>ለቁፋሮ ሥራዎች የአካባቢ፣ የጤንነት እና የደህንነት መስፈርቶች</u>

፩/ ባለፈቃዱ የቁፋሮ ሥራዎቹን በሚከተለው መልኩ ማከናወን አለበት፡-

ሀ) ከመሬት ላይ ወይም ከከርሰምድር የሚገኝ ውሃ፣ አየር፣ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የዱር አራዊት፣ አፈር፣ ዕጽዋት እና ታሪካዊ ቦታዎችን የመጠበቅ፣

ለ) ባህላዊ እሴቶችን፣ ውብ ተፈጥሯዊ ቦታዎችን እና የመዝናኛ ሀብቶችን መጠበቅ፣

ሐ) ከሥራው ጋር የተያያዙ የድምፅ ሁከትን መቀነስ፣

መ) የንብረት ማጥፋትን እና አስፈላጊ ያልሆነ የመሬት ጉዳትን መከላከል፡፡

፪/ ባለፈቃዱ በሥራ ላይ የማይገኙ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ማስወገድ ወይንም በተገቢው ሁኔታ ማስቀመጥ አለበት፡፡

፫/ ባለፈቃዱ ከቁፋሮ እና ከጉድጓዶች ፍተሻ የሚወጡ ፈሳሾችን በተገቢ ሁኔታ በተዘጋጁ በማቆሪያ ጉድጓዶች ወይም ታንከሮች ማስቀመጥ አለበት፡፡

፬/ ባለፈቃዱ የማቆሪያ ጉድጓዶቹ የማያስፈልጉት ከሆነ ቦታውን ፈቃዱን በወሰደበት ጊዜ ወደነበረበት ወይም ወደ ተሻለ ሁኔታ መመለስ አለበት፡፡

፭/ ባለፈቃዱ በአካባቢ ጥበቃ መስፈርቶች መሠረት ችግር ሲያጋጥም በአካባቢው ላይ የሚከሰተውን ማንኛውንም ተፅዕኖ ለመቀነስ ወዲያውኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

6/ Monitor activities during all drilling operations, establish a system to follow up each well drilling from start to finish for daily activity report , and submit such reports as required by the Licensing Authority;

7/ Keep the well under control at all times; and

8/ Conduct safety meetings regularly.

45. <u>Environmental, Health and Safety Requirements for Drilling Operations</u>

1/ The Licensee must conduct its drilling operations to:

a) protect the quality of surface and subsurface water, air, natural resources, wildlife, soil, vegetation, and Historical places;

b) protect the quality of cultural, scenic, and recreational resources;

c) minimize noise related to the activity; and

d) prevent property damage and unnecessary degradation of the lands.

2/ The Licensee must remove or, properly store all equipment and materials that are not in use;

3/ The Licensee must retain all fluids from drilling and testing the well in properly designed pits, or tanks;

4/ When the Licensee no longer needs a pit , it must abandon it and restore the site to conditions as good as or better prior to the license period;

5/ In the event of exceedance of environmental standards or requirements, the Licensee must immediately take steps to abate the exceedance and mitigate any impacts on the environment;

፮/ ባለፈቃዱ ለሥራው የሚጠቀምባቸውን አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች እና ፈንጂዎች ለሥራው በሚያስፈልገው መጠን ብቻ መጠቀም ሲኖርበት በሚያጓጉዝበት እና በሚያከማችበት ጊዜ የዓለም አቀፍ መርሆዎችና ምርጥ ተሞክሮዎችን እና የኢትዮጵያን የሕግ ማዕቀፎች መከተል ይጠበቅበታል፡፡

፯/ ባለፈቃዱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና ለአከባቢው መስተዳድር አካላት ወድያውኑ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) ጉድጓዱ ከቁጥጥር ውጪ ከሆነ፣

ለ) በፈቃድ ቦታው እና በአካባቢው በሰው ላይ የሚደርሱ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ጨምሮ በሰው እና በማህበረሰቡ ላይ አደጋ ያስከተሉ ወይም ሊያስከትሉ የሚችሉ አጋጣሚዎችን፤

ሐ) ወደ አካባቢ የሚለቀቁ በዓይነት ወይም በመጠን ለአካባቢው ጎጂ የሆኑ ንጥረ ነገሮች፡፡

፰/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የደህንነት ቁጥጥር ፕሮግራም ሊያወጣ የሚችል ሲሆን ይህም የደህንነት ተቆጣጣሪን በመሰየም በጤናና ደህንነት መስፈርት መሠረት መከናወኑን ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡

፱/ ፈቃዱን ለማፅደቅ ከቀረበው የጤናና ደህንነት ዕቅድ በተጨማሪ ባለፈቃዱ የህዝቡን ጤንነትና ደህንነት፣ የሰራተኛውን ደህንነት ወይንም አካባቢ ላይ ለሚደርስ አደጋ ፈጣን እና ውጤታማ የአስቸኳይ አደጋ ምላሽ የሚሰጡ የአስቸኳይ ጊዜ አፈጻጸም አሰራሮችን እንዲያቀርብ ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ፵፮. የአካባቢ ፈንድ ስለመመደብ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፰ (፪) መሠረት ባለፈቃዱ ለዚህ ዓላማ በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የአካባቢ ፈንድ ማስቀመጥ አለበት፡፡

፪/ በባለፈቃዱ የሚቀመጠው የገንዘብ መጠን የሚወሰነው በፀደቀው የአካባቢያዊ እና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት መሠረት ሲሆን ለምርመራና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ ለየፕሮጀክቱ ጠቅላላ ሥራ ከሚወጣው ወጪ ከ0.1 በመቶ (0.1%) ያነሰ መሆን አይችልም፡፡

6/ The Licensee must minimize the volume of any hazardous chemicals and explosives on site to that amount necessary for efficient operations and must transport, manage and store consistent with international standards and best practices and the laws of Ethiopia;

7/ The Licensee must immediately report to the Licensing Authority and the local authorities in the happening of:

a) loss of control of the well;

b) all incidents or accidents resulting in or potentially threatening harm, including injury or death, to persons in the License Area or nearby communities; and

c) discharges to the environment of materials of types or in volumes detrimental to the environment.

8/ The Licensing Authority may establish a safety inspection program, including a designated safety inspector, to ensure compliance with health and safety requirements,

9/ In addition to any health and safety plans required as a condition of license approval, the Licensing Authority may require the Licensee to prepare an emergency response plan or contingency plan showing how the Licensee will respond to emergency situations threatening the public health and safety, worker safety, property, or the environment.

## 46. Allocation of Environmental Fund

1/ In accordance to Article 38 (2) of the Proclamation, the Licensee must deposit an environmental fund in a closed bank account opened for such purpose,

2/ The amount of the fund to be deposited by the Licensee shall be determined by the approved Environmental and Social Impact Assessment Study, but shall not be less than 0.1% of the overall costs of the project activities covered by the Exploration or Well-Field Development and Use License,

፫/ ባለፈቃዱ ለፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ፈንዱን ስለማስቀመጡ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## ፵፯. የአካባቢ ፈንድ ስለመልቀቅ

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባለፈቃዱ የአካባቢ ፈንዱ እንዲለቀቅለት በሚጠይቅበት ጊዜ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ይለቅለታል፡-

፩/ ፈቃዱ ከተቋረጠ ወይም ከተሰረዘ እና ባለፈቃዱ የፍቃድ ቦታውን ፈቃዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበረበት ወይም ወደተሻለ ሁኔታ መልሶ ካስተካከለ፡ ወይም

፪/ ፈቃዱ ወደ ሌላ ሰው ከተላለፈ እና ተመሳሳይ መጠን ያለው ፈንድ በአዲሱ ባለፈቃድ ከተተካ፡፡

## ፵፰. ማስረጃ ስለማረጋገጥ

፩/ ሁሉም የቁፋሮ ሰራተኞች የቁፋሮ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ በተገቢው ሁኔታ የተረጋገጠ የትምህርት ማስረጃ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ማስረጃው በ የሁለት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

፪/ የጉድጓድ መዝጊያውን ማገናኛ መበየድ የሚገባው የበያጅነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው በያጅ መሆን የሚገባው ሲሆን የሚበየድበት ዕቃዎችም ለዚሁ ተግባር በተወሰነው መመሪያ መሠረት መሆን ይገባዋል፡፡

## ፵፱. የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ጉድጓድ ቁፋሮ ወደ ደረጃ 1 የሚተላለፍበት ሁኔታ

፩/ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የተሰጠ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታ በቁፋሮ ጊዜ ያለውን ሙቀት ከሚፈለግበት ነጥብ ጥልቀት በአስር ዲግሪ ሴልሺየስ ሊደርስ እንደሚችል ወይም ከደረሰና ከአካባቢው ውሃ ልክ ጋር ሲታይ ወዲያውኑ የቁፋሮ ሥራውን በማቆም ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በማሳወቅ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ በሚካሄድበት ሂደት መከናወን ይገባዋል፡፡

3/ the Licensee shall submit to the Licensing Authority evidence regarding the deposit of such fund.

## 47. Release of Environmental Fund

The Licensing Authority will release the environmental fund upon request by the Licensee if the Licensing Authority determines that:

1/ the License has been terminated or revoked and the Licensee has restored the license area to conditions as good as or better than conditions prior to the license period; or

2/ the License is transferred to another person and the fund is replaced by the same amount by the new license holder.

## 48. Certifications

1/ All tool pushers, drilling superintendents, are required to have completed an internationally recognized well control certification program and furnish the certification of satisfactory of completion to the Licensing Authority prior to the start of any drilling operations. The certification must be renewed every two years.

2/ Welding of wellhead connections must be performed by a certified welder who has certificate of Competence using materials in conformance with directives established for this purpose.

## 49. Transfer of Drilling of Grade II Geothermal Resource Wells to Grade One

1/ a condition that in the following circumstance, a holder of a Grade II Geothermal Resources License issued by either the Licensing Authority or a State shall immediately cease drilling operations and shall notify the Licensing Authority: if a well reaches, or may reasonably be expected to reach, a downhole temperature within 10°C of the boiling point for depth (BPD) as measured from the local water level; in that event, the Licensing Authority shall immediately assume responsibility for oversight of drilling operations, including an assessment of the potential applicability of

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጹት ክስተቶች ሲኖሩ ባለፈቃዱ ፕሮጀክቱን የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባስቀመጠው መስፈርት ሊቀጥል ይችላል ወይም ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ በአዋጁና ደንቡ መሠረት ማልማት ይችላል፤ ካልሆነም የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃዱንና ይዞታውን መመለስ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚመለከተው የክልል መንግሥት የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ላይ የሚከናወኑ የቁፋሮ ሥራዎች የምስክር ወረቀትን ጨምሮ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ አሰራር ሂደትን ተከትሎ ይከናወናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች

### ፶. ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፬ መሠረት በጂኦተርማል አማካሪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም አመልካች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል:-

ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

(፩) ሙሉ ስሙን፣ጾታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣የትውልድ ቀንና ቦታ፣

(፪) የመታወቂያ ቅጂ፣

(፫) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

(፬) ሙያውን፣

Grade I Well-field Development and Use License drilling standards, and shall provide notice of its assumption of authority and additional direction to the State and the Licensee, with a request for relevant records.

2/ a condition that upon the occurrence of circumstances described in Sub-Article (1) of this Article, the Licensee may continue its project consistent with requirements established by the Licensing Authority, or apply for a Grade I Well-field Development and Use License in accordance with the provisions of the Proclamation and the regulations, or surrender its Grade II Geothermal Resources License and any right to use geothermal resources or the land included in the license area.

3/ Subject to the limitations in Sub-Article (1) and (2) of this Article, drilling of wells under Grade II Geothermal Resources Licenses issued by either a State or the Licensing Authority shall be subject to the rules for development of water wells, including certification requirements for water well drillers.

## PART SEVEN

## CERTIFICATE OF COMPETENCE

### 50. Application for a Certificate of Competence

1/ Subject to Article 34 of the Proclamation, any application submitted for a Certificate of Competence in geothermal consultancy services by a professional, shall contain the following:

a) Where the applicant is a natural person:

(1) full name, nationality, gender, nationality, place and date of birth

(2) Copy of identity card

(3) country of residence and address, telephone number and email address

(4) Profession

(፭) የትምህርት ማስረጃ ቅጂ እና በመመሪያ በሚገለጸው መሠረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ ቅጂ፤

(፮) የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የጠየቀበትን የሙያ ዘርፍ፤

(፯) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች፡፡

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ፡-

(፩) ስሙን ፣ ዜግነቱን ፣ የሕግ አቋሙንና የንግድ ሁኔታ፤

(፪) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤

(፫) በድርጅቱ የተቀጣሪ ባለሙያዎች የትምህርት፣ የሥራ ውል እና በመመሪያ በሚገለጸው መሠረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ፤

(፬) አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፤

(፭) በአመልካቹ ድርጅት ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠውን ኃላፊ ስም እና ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤

(፮) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፤

(፯) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሀ) ስር ከ(፮) እስከ (፯) የተጠቀሱትን መረጃዎች፡፡

፪/ በጂኦተርማል ለቴክኒክ ነክ ሥራዎች ለሚሰጡት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አመልካች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡

ሀ) ስሙን ፣ ዜግነቱን ፣ የሕግ አቋሙን ፣ የንግድ ሁኔታ፤

ለ) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤

(5) the copies of necessary educational qualification documents and work experience as specified in the directive to be issued;

(6) discipline for which certificate of professional competence for consultancy service is requested;

(7) Any other additional information determined in the directive of the Licensing Authority.

b) Where the applicant is a juridical person:

(1) its name, nationality, legal form, and nature of business;

(2) address of its head office, telephone number, and email address;

(3) employee profiles such as education, work experience and employment contract as specified in the directive;

(4) copies of its memorandum and Articles of Association duly certified by the appropriate government organization;

(5) the name, position, telephone number and email address of an official authorized to sign on behalf of the applicant business organization;

(6) if the applicant is a foreigner, a license authorizing the carrying on of business in Ethiopia;

(7) particulars stated from (6) to (7) under Sub-Article (1) (a) of this Article.

2/ Any application submitted for a Certificate of Competence for geothermal technical works by a juridical person, shall contain the following:

a) Its name, nationality, legal form, nature of business;

b) Address of its head office, telephone number, and email address;

ሐ) በድርጅቱ የተቀጣሪ ባለሙያዎችን የትምህርት፣ የሥራ ውል እና በመመሪያ በሚገለጸው መሠረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

መ) አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣

ሠ) በአመልካቹ ድርጅት ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠውን ኃላፊ ስም እና ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

ረ) የውጭ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፣

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፊደል ተራ (ሀ) ስር ከ(፮) እስከ (፯) የተጠቀሱትን መረጃዎች፣

ሸ) የጂኦተርማል የቴክኒክ ነክ ሥራዎች ወይም ለጂኦተርማል ምክር አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጠየቀበትን ዘርፍ፣

ቀ) የተገለጸውን ሥራ ለመፈፀም የሚያስችል ቴክኒካዊ እና የገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ መረጃ፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የጂኦተርማል የቴክኒክ ነክ ሥራዎች ብቃት እና የጂኦተርማል የማማከር የምስክር ወረቀት በየሙያው ዘርፉ ሊለያይ ይችላል፡፡

## ፶፩. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶ (፩) እና (፪) መሠረት ተሚልቶ የቀረበ ማመልከቻ ተገቢው የማመልከቻ ክፍያ እንደተፈፀመ ይመዘገባል:

፪/ ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ ባሉት አስር (፲) የሥራ ቀናት ውስጥ በመመሪያው በሚወሰነው መስፈርት መሠረት የሚያሟላ መሆኑን በማጣራትና በመገምገም የምስክር ወረቀት ይሰጣል ወይንም የማያሟላበትን ምክንያት በጽሁፍ በመግለጽ ሊከለክል ይችላል፡፡

## ፶፪. <u>የብቃት ማረጋገጫ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜና ዕድሳት</u>

፩/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሁለት ዓመት የፀና ይሆናል፡፡

c) employee profiles such as education, work experience and employment contract as specified in the directive;

d) copies of its memorandum and Articles of Association duly certified by the appropriate government organization;

e) the name, telephone number and email address of an official authorized to sign on behalf of the applicant business organization;

f) if the applicant is a foreigner, a license authorizing the carrying on of business in Ethiopia;

g) particulars stated from (6) to (7) under Sub-Article (1) (a) of this Article;

h) discipline for which certificate of professional competence for geothermal technical works or geothermal consultancy service is requested;

i) information related to the technical and financial capacity of the applicant to carry out the work discipline requested,

3/ The Licensing Authority may, through a directive, issue a classification of Certificates of Competency for geothermal consultancy and geothermal technical works.

## 51. <u>Issuance of Certificate of Competence</u>

1/ An application that meets the requirements provided under Article 50 (2) and (3) of this Regulation shall be registered upon the payment of the prescribed application fee.

2/ The licensing authority may issue the certificate applied for within ten (10) working days after receipt of the application after examining and ensuring that the applicant meets the requirements issued by the directive or notify the applicant, in writing of the rejection and the reasons thereof.

## 52. <u>Validity and Renewal of a Certificate of Competence</u>

1/ A Certificate of Competence shall remain valid for a period of two (2) year.

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የቆየበት ጊዜ ካለቀ በኋላ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ዕድሳቱን የሚፈጽመው ባለፈቃዱ በገባው ግዴታና መለኪያ መሠረት ማከናወኑን ካረጋገጠ በኋላ ይሆናል፡፡

፬/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሠረት የሙያው ሥነ-ምግባርና የቴክኒክ ብቃቱ የሚጠይቀውን ግዴታ ያልተወጣ መሆኑ ከተረጋገጠ የምስክር ወረቀቱ አይታደስም፡፡

፭/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የዕድሳት ማመልከቻውን ካልተቀበለ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፶፫. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚከተሉት ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫውን ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተሳሳተ ማስረጃ በማስገባት የተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የጂኦተርማል ዘርፉ የሚጠይቀውን ወቅታዊ ብቃትና ቴክኖሎጂ ያገናዘበ እንዲሁም ሙያዊ ሥነ-ምግባርን ያሟላ አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከተረጋገጠ የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን ከማለቁ በፊት ሊሰረዝ ይችላል፣

ሐ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው የዚህን ደንብ ወይም ደንቡን ለማስፈፀም የወጡትን መመሪያዎች ድንጋጌዎች ወይም መመሪያዎች ካላከበረ ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከተቀበለ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃዎችን ካልወሰደ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

2/ A Certificate of Competence shall be renewed annually starting from the end of its validity date.

3/ The licensing authority renews the certificate of competence upon request, after ascertaining that the performance is in compliance with the obligations and standard required.

4/ The certificate of competence shall not be renewed, if the Licensing Authority proves that the applicant has failed to comply with professional ethics and technical obligations in accordance with the terms of his Certificate of Competence.

5/ If the licensing authority rejects an application for renewal of a Certificate of Competence, it shall inform to the applicant within ten (10) working days in writing.

## 53. Revocation of a Certificate of Competence

1/ The Licensing Authority may revoke the Certificate of Competence on any of the following grounds:

a) Where the certificate of competence is proved to have been obtained by submitting false evidence;

b) Where the Licensing Authority proves that the holder of a Certificate of Competence failed to carry out his duties in an ethical manner and to use modern technology and good practice generally accepted in the geothermal sector, the Licensing Authority may revoke the certificate prior to the expiry of the validity period.

c) Where the holder of the Certificate of Competence fails to comply with the provisions of this Regulation or directives issued for the implementation of this Regulation or to take corrective measures within one month following a written notice given to it by the licensing authority.

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ከተሰረዘበት ከአንድ ዓመት በኋላ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ሆኖም አመልካቹ ፈቃዱ ለመሰረዙ ምክንያት የነበሩትን ቀደምት ስህተቶች ማስተካከል እና በፈቃድ ሰጭ ባለስልጣን የተቀመጠውን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

፫/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ወይም ሥራውን ያቆመ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫውን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን መመለስ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት
## ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች

**፶፬. አንደኛ ደረጃ ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች፡-**

፩/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በቅድሚያ ተገቢውን ፈቃድ ሳይዝ በጂኦተርማል ሥራ ላይ ከተሰማራ፣

ለ) ከፈቃድ ማመልከቻ ወይም ፈቃድ ወይም ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄና እድሳት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠ ወይም ካጭበረበረ፣

ከሁለት መቶ ሺህ (፪፻ ሺ.) ብር እስከ ሶስት መቶ ሺህ (፫፻ ሺ.) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

ሀ) የጂኦተርማል ሥራውን በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት፣ ቴክኖሎጂውና የጂኦተርማል ኢንደስትሪው ተቀባይነት ባገኘ አሰራር ልምድ ካላከናወነ፣

ለ) ዘላቂነት በሌለው መልኩ እና ከሪዘርቫየር ኢንጅነሪንግ ሪፖርት ጋር ወጥነት የሌለው የጂኦተርማል ሥራ ካከናወነ፣

ሐ) ከፈቃድ መብቱ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የማጭበርበር ድርጊት ከፈጸመ፣ ወይም ከጂኦተርማል ሥራው ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠ፣

2/ Any person, whose certificate of competence has been revoked, may request for a new certificate of competence one (1) year after the revocation, provided that the applicant has amended the previous faults that were the ground for the revocation and fulfills all requirements set by the Licensing Authority.

3/ Any person whose Certificate of Competence has been revoked or who has ceased operating his activity shall return the Certificate of Competence to the licensing Authority.

## PART EIGHT
## FUALTS AND ADMINISTRATIVE MEASURES

**54. First Level Faults and Administrative Measures**

1/ Any person who:

a) undertakes geothermal operation without having obtained the appropriate license;

b) makes a false statement or fraudulent misrepresentation in connection with an application or relating to a license or certificate of competence;

shall be punishable with a fine from Two Hundred Thousand (200,000) Birr up to Three Hundred Thousand (300,000) Birr.

2/ Any Licensee who:

a) carry out geothermal operations not in accordance to Proclamation, this Regulation and Directives issued hereunder with technology and geothermal operations consistent with best practice generally accepted in geothermal industry;

b) conducts geothermal operations in an unsustainable manner, inconsistent with the reservoir engineering;

c) commits any kind of fraudulent act in relation to rights emanated from a license or has submitted false information or commits fraudulent act in connection with geothermal operations;

መ) የተፈጥሮ አካባቢን፣ጤንነትን፣ደህንነትን፣ ወይም ሌሎች የጂኦተርማል ሥራዎችን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ከጣሰ፣ ወይም

ሠ) በተጨባጭ ሁኔታ የጂኦተርማል ሥራዎችን የሚመለከቱ አስተዳደራዊና የገንዘብ ግዴታዎችን ካላሟላ፣

ከአንድ መቶ ሺህ (፩፻ ሺ.)ብር እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ (፩፻፶ ሺ.) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ እንዲሁም አጥፊው ያንኑ ጥፋት ደግሞ ከፈጸመ የገንዘብ ቅጣቱ በእጥፍ ሊጨምር ይችላል፡፡

## ፶፭. <u>ሁለተኛ ደረጃ ጥፋቶች እና ቅጣቶች</u>፡-

ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

፩/ እንደአግባቡ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፰ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ተፈላጊ መዝገቦችና ሪከርዶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን በተገቢው መልኩ ካልያዘ ወይም መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችንና ሪከርዶችን ከያዘ ወይም ተፈላጊ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን ካልሰጠ፣

፪/ በአግባቡ ስልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሠራተኛን ወደ ፈቃዱ ክልል ወይም የጂኦተርማል ሥራዎች የሚካሄዱባቸው ቦታዎች ወይም ተቋሞች እንዳይገባ ከከለከለ ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ሪከርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈጸመ፣

፫/ የማማከር እና የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የጂኦተርማል ዘርፉ የሚጠይቀውን ወቅታዊ የሙያ ብቃትና ቴክኖሎጂ ያገናዘበ እንዲሁም ሙያዊ ሥነ ምግባርን ያሟላ አገልግሎት መስጠት ካልቻለ፣

d) commits violations of obligations relating to environment, health, safety or other geothermal operations; or

e) fails materially to meet administrative and fiscal obligations of geothermal activities;

shall be fined from One Hundred Thousand (100,000) Birr up to Three Hundred Thousand (150,000) Birr if the person commits another act or omission which constitutes a further such infraction, the amount of the fine may be doubled.

## 55. <u>Second Level Fault and Administrative Measures</u>

A Licensee who:

1/ fails to maintain, as the case may be, books and records or other documents or materials required under Article 28 of this Regulation or maintains books and records which are materially incorrect or incomplete, fails to file reports or other documents or fails to give notices required;

2/ fails to grant a duly authorized official of the Licensing Authority entry into the license area, the area covered by a license or access to any other site or premises of the geothermal operations or to his books, records, other documents or materials, or fails to carry out a lawful order or instruction of such official;

3/ where the holder of a certificate of competence for consultancy and technical service failed to carry out his duties in an ethical manner, to use modern technology and generally accepted geothermal operation practices of the geothermal sector.

የፈጸመውን የጥፋት ድርጊት ለማረም ወዲያውኑ እርምጃ ከወሰደ ከሃምሳ ሺህ (፶ ሺ.) ብር እስከ ሰማንያ ሺህ (፹ ሺ.) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡ ጥፋቱን ለማረም ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ የገንዘብ ቅጣቱ እጥፍ ይሆናል፤ ጥፋቱ በማንኛውም ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት፣ በተፈጥሮ አካባቢ ወይም በጂኦተርማል ሀብቱ ላይ ሊደርስ የተቃረበ ወይም ቀጣይነት ያለው ጉዳት ካስከተለ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባለፈቃዱ ጥፋቱን እስከሚያስተካክል ድረስ የጂኦተርማል ሥራዎቹን ወዲያውኑ እንዲያቆም ያደርጋል፤ የጥፋቱ ድርጊት ወይም ሁኔታ እስኪስተካከል ፈቃዱ ታግዶ ይቆያል፡፡

**፶፮. ሶስተኛ ደረጃ ጥፋቶች እና ቅጣቶች፡-**

ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

፩/ መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን የመያዝ ጉድለቶችን ሳይጨምር የተሟሉ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታን የሚያሳዩ መዝገቦችንና ሪከርዶችን ካልያዘ፣

፪/ ተፈላጊ ሪፖርቶችንና ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ መግለጫዎችን በወቅቱ ካልሰጠ፣ ወይም

፫/ ጥፋቱ የማንኛውንም ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት፣ የተፈጥሮ አካባቢን ወይም የጂኦተርማል ፈሳሽ ክምችቱን አደጋ ላይ የማይጥል ቢሆንም የጂኦተርማል ሥራዎቹን ተገቢ በሆነ መንገድና በጥንቃቄ ካላካሄደ ወይም ደንቦችንና መመሪያዎችን ካላከበረ፣

ማስጠንቀቂያ እንደደረሰው ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ ወይም የጥፋት ድርጊቱ ሊታረም የማይችል ከሆነ ከሰላሳ ሺህ (፴ ሺ.)ብር እስከ ሃምሳ ሺህ (፶ ሺ.) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

shall be fined from Fifty Thousand (50,000) Birr up to Eighty Thousand (80,000) Birr, if immediately takes remedial action to correct the violation after receiving notice; if the person concerned does not take remedial action immediately, the amount of the fine shall be doubled; if the violation results in an imminent or continuing danger to the health and safety of any person, the environment or the geothermal resource, the Licensing Authority may immediately order suspension of geothermal operations license pending the correction of the violation, and the license shall be suspended until such act, omission or condition is rectified.

**56. Third Level Faults and Administrative Measures**

Any Licensee who:

1/ fails to maintain his books and records in a complete, accurate and current manner, excluding such deficiencies which are materially incorrect or incomplete.

2/ fails in a timely manner to file all reports and other documents or to give notices required; or

3/ fails to carry out geothermal operations in a proper and prudent manner or to observe regulations or directives, but which failure does not endanger the health or safety of any person, the environment or the geothermal reservoir.

shall be punishable with a fine from Thirty Thousand (30,000) Birr up to Fifty Thousand (50,000) Birr if fails to take remedial measure to correct the violation immediately after receiving notice.

፬/ ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተፈፀመ ጥፋት የቀጣይነት ወይም የተደጋጋሚነት ባህርይ ያለው ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ጥፋቱን እንደቅደም ተከተሉ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ጥፋት አድርጎ ሊቆጥረውና ባለፈቃዱም በዚሁ ሊቀጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፯. ከጂኦተርማል ጋር የተያያዙ ናሙናዎችን ወደ ውጪ ስለመላክ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፴ መሠረት ማንኛውም የጂኦተርማል ሥራ ባለፈቃድ የጂኦተርማል ናሙናዎች ለላቦራቶሪ ምርመራ ወደ ውጪ አገር መላክ የሚችለው ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በማስፈቀድ እና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም ይሆናል፡፡

፪/ አመልካቹ በምርምር ተቋማት የሚሠራ ወይም በውጪ አገር ከፍተኛ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኝ ሰው ከሆነ የጂኦተርማል ናሙናዎቹ ለትምህርታዊ ምርምር አስፈላጊ መሆናቸውን የሚገልጽ አግባብ ካለው ተቋም የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ በአዋጁ አንቀፅ ፴ (፪) መሠረት የጂኦተርማል ናሙና ለመላክ ለሚፈልግ የጂኦተርማል ሥራ ባለፈቃድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) ከፍተኛ ሙቀት ካላቸው ጉድጓዶች፣ ሞቃታማ ምንጮች እና የሞቀ ውኃ ጉድጓዶች በአንድ ነጠላ ናሙና ከፍተኛው አምስት (፭) ሊትር ፈሳሽ፣

ለ) በአንድ ጉድጓድ እስከ ሁለት ነጥብ አምስት(፪.፭) ቶን ኮር ወይም የድንጋይ ናሙና፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ ደንብ እና በሚወጣው መመሪያ መሠረት ከጂኦተርማል ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናሙናዎችን ለመላክ ሊወስን ይችላል፡፡

4/ If any act or omission which constitutes on Sub-Article (2) and (3) of this Article of a continuing or repeated nature, the Licensing Authority may deem it to constitute a first level offence or a secondary offence respectively, and the Licensee concerned shall be subject to the applicable penalties.

## PART NINE

## MICELLANEOUS

### 57. Export of Geothermal Related Samples

1/ In accordance to Article 30 of the Proclamation, any licensee, by the permission of the Licensing Authority and upon payment of prescribed fees, may export geothermal samples as appropriate, to conduct laboratory testing or analysis.

2/ if the applicant is an employee of the research institute or a student of higher education abroad has to submit original copy of recommendation letter from appropriate organization that confirms geothermal samples to be exported are necessary for research,

3/ Subject to Article 30 (2) of the Proclamation, a geothermal licensee wishing to export geothermal samples shall fulfill the following requirements:

a) For fluid sample from high temperature wells, hot springs and hot water wells a maximum volume of 5 liter of fluid per single sample.

b) Maximum 2.5 tone of core or rock sample per well.

4/ The licensing authority may determine other related aspects of export of geothermal samples in accordance to this Regulation and directives to be issued hereunder.

## ፶፰. ስለቅጥርና ሥልጠና

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ (፩) ፊደል ተራ (ሸ) ስለቅጥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ አንድን የሥራ መደብ ለመሙላት ብቁ የሆነ ኢትዮጵያዊ ማግኘት አለመቻሉን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አረጋግጦ ፈቃድ ሲሰጥ ብቁ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሊቀጥር ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀጠሩት የውጭ አገር ዜጎችና ቤተሰቦቻቸው ወደ አገር ውስጥ የመግቢያና የመኖሪያ ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት መስሪያ ቤት እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የውጪ አገር ዜጋ እንዲቀጥር የተፈቀደለት ባለፈቃድ አግባብ ያለው ክህሎትና ዕውቀት የሚተላለፍለት ተተኪ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ አብሮ የሚሠራበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

፬/ የውጭ አገር ዜግነት ያለው ባለሙያ ዕውቀቱንና ክህሎቱን ለኢትዮጵያዊ ሠራተኛ በበቂ ሁኔታ ለማስተላለፍ የሠራበት ጊዜ በቂ መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በክትትል ሂደት ሲያረጋግጥ ባለፈቃዱ የውጪ አገር ዜጋውን በኢትዮጵያዊ ባለሙያ መተካት አለበት፡፡

፭/ የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታና ሥልጠና አሠጣጥ ከሥራው ባህርይና ደረጃ ጋር የተጣጣመ እንዲሁም ሥራውን በተቀላጠፈና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ማካሄድ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

## ፶፱. የፈቃድ ክፍያዎች

ፈቃድ ለማውጣት የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ ፵፭ መሠረት የሚከፍለው የፈቃድ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩/ የቅኝት የማመልከቻ ክፍያ ...............፭፻ ብር

፪/ የምርመራ የማመልከቻ ክፍያ ............፭፻ ብር

፫/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ የማመልከቻ ክፍያ...፭፻ብር

፬/ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት የማመልከቻ ክፍያ..........................................፭፻ ብር

፭/ የቅኝት የፈቃድ ክፍያ ...................፬ ሺ. ብር

## 58. Employment and Training

1/ without prejudice to paragraph (h) of Article 22(1) of the Proclamation, any licensee may employ a qualified foreign national, if provides evidence that shows a qualified Ethiopian national cannot be found to fill a position and obtains approval and permission thereof from the Licensing Authority.

2/ the Licensing Authority shall provide support to the licensee in order to obtain from concerned government office entry and residence permit for foreign nationals and their dependents in Ethiopia.

3/ a licensee who has obtained a permission to employ a foreign national, in accordance with Sub-Article (1) of this Article, shall facilitate a condition for a foreign national to work with and to transfer his skills and knowledge to an Ethiopian national.

4/ the foreign national shall be replaced by Ethiopian national where it is verified by the Licensing Authority that the foreign national has been working for enough time to transfer his skills and knowledge to an Ethiopian national.

5/ the employment condition and training provided shall commensurate with the nature and extent of operation; and the operation shall be conducted in efficient and economic manner.

## 59. License Fees

The license fees to be paid by an applicant for a license pursuant to Article 45 of the proclamation shall be as follows:

1/ Reconnaissance Application Fee ...500 Birr

2/ Exploration Application Fee .......500 Birr

3/ Grade I Well-field Development and Use Applicalication Fee ....................500 Birr

4/ Grade II Geothermal Resources Application Fee .......................................500 Birr

5/ Reconnaissance License Fee ......4,000 Birr

፮/ የምርመራ የፈቃድ ክፍያ ...............፭ሺ.፶ ብር

፯/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስከ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ ክፍያ ......፱ሺ.፭፻፷ብር

፰/ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት የፈቃድ ክፍያ..... ..............................................፭ሺ.፶ ብር

## ፷. የፈቃድ እድሳት ክፍያ

ፈቃድ ለማደስ የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ ፵፭ መሰረት የሚከፍለው የፈቃድ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩/ የምርመራ ፈቃድ እድሳት ክፍያ .....፫ሺ.፫፻፳ብር

፪/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስከ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ የእድሳት ክፍያ... ፯ ሺ. ብር

፫/ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ እድሳት ክፍያ....................................፫ሺ.፫፻፳ ብር

## ፷፩. የምትክ ወይም ተጨማሪ የፈቃድ ቅጂ ክፍያ

በባለ ፈቃዱ ለጠፋ፣ የተቃጠለ፣ የተበላሸ፣ የተሰረቀ ወይም ተጨማሪ የፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ቅጂ የሚከፈለው ክፍያ የሚከተሉት ናቸው:

፩/ የቅኝት ፈቃድ የምስክር ወረቀት ........፫፻ ብር

፪/ የምርመራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት......፫፻ ብር

፫/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስከ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ የምስክር ወረቀት.. ፫፻ብር

፬/ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የምስክር ወረቀት ....................................፫፻ ብር

፭/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት....፫፻ ብር

፯/ ሌላ ሰነድ በገጽ ............................ ፫፻ ብር

## ፷፪. ፈቃድ የማስተላለፊያ ክፍያ

በባለ ፈቃዱ የሚከፈል የፈቃድ ለውጥ ክፍያ የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ የምርመራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት.... ፩ሺ.፲ ብር

፪/ ለደረጃ I የጂኦተርማል ጉድጓድ መስከ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ................ ፩ሺ.፲ ብር

፫/ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የምስክር ወረቀት ..................................... ፩ሺ.፲ ብር

6/ Exploration License Fee ....5,050 Birr

7/ Grade I Well-field Development and Use License Application Fee .........9,560 Birr

8/ Grade II Geothermal Resources License Fee ....................................5,050 Birr

## 60. License Renewal Fees

The license renewal fees to be paid by an applicant for a license pursuant to Article 45 of the proclamation shall be as follows:

1/ Exploration License Renewal Fee...3,320 Birr

2/ Grade I Well-field Development and Use License Renewal Fee ..............7,000 Birr

3/ Grade II Geothermal Resources License Renewal Fee .........................3,320 Birr

## 61. License Replacement or Additional Fees

The license replacement fees to be paid for lost, burnt, damaged, stolen or additional license or certificate by a license holder are as follows:

1/ Reconnaissance License Certificate .300 Birr

2/ Exploration License Certificate ......300 Birr

3/ Grade I Well-field Development and Use Application License Certificate .....300 Birr

4/ Grade II Geothermal Resources License Certificate ..............................300 Birr

5/ Certificate of compétence............300 Birr.

6/ Other Documents per Page ...........50 Birr

## 62. License Transfer Fees

The license transfer fees to be paid by a license holder are as follows:

1/ Exploration License Certificate ....1,010 Birr

2/ Grade I Well-field Development and Use Application License Certificate ..1,010 Birr

3/ Grade II Geothermal Resources License Certificate ...........................1,010 Birr

**፷፫. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ክፍያ**

፩/ የማማከር አገልግሎት የምዝገባ ክፍያ...፩፻ ብር

፪/ የቴክኒክ ነክ አገልግሎት የምዝገባ ክፍያ ...... ........................................... ፩ሺ.፲ ብር

፫/ የማማከር አገልግሎት የፈቃድ ክፍያ ፬፻ ብር

፬/ የቴክኒክ ነክ አገልግሎት የፈቃድ ክፍያ...... ..............................................፪ሺ፮፻፶ ብር

፭/ የማማከር አገልግሎት የእድሳት ክፍያ ...፪፻ ብር

፮/ የቴክኒክ ነክ አገልግሎት የእድሳት ክፍያ ፪፻ ብር

**፷፬. ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች**

በባለ ፈቃዱ የሚከፈል ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ የናሙና መላኪያ

ከ፲ ኪሎ በታች በጥቅል ...............፶ ብር

ከ፳ ኪሎ በታች በጥቅል...............፩፻ ብር

፳ ኪሎ እና ከዚያ በላይ በጥቅል......፪፻ ብር

፪/ የጉድጓድ ቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ በጉድጓድ....... ..................................................፩ሺ. ፶ብር

**፷፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ዶ/ር አብይ አህመድ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**63. Competence Certificate Service Fee**

1/ Professional Consultancy Service Registra tion Fee ..............................100 Birr

2/ Technical Service Registration Fee 1,010 Bir

3/ Professional Consultancy Service Licensee Fee ..................................400 Birr

4/ Technical Service License Fee.....2,650 Birr

5/ Professional ConsultancyService Renewal Fee.................................200 Birr

6/ Technical Service Renewal Fe.....200 Birr

**64. Various Services Fees**

Fees to Paid by the Licensees for Various Services

1/ Sample Export

Below 10 kg per package ......... 50 Birr

Below 20 kg per package .........100 Birr

20 kg or above per package........200 Birr

2/ Payment for Drilling Permit per Well.... .........................................1,050 Birr

**65. Effective Date**

This regulation shall enter into force up on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa on this 22nd Day of July, 2019.**

**Dr. ABIY AHMED**

**PRIME MINISTER OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**